
# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 077 ኅዳር 17 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# “የአፍሪካ ሀገራት ትብብርና አጋርነት ለአሕጉሪቱ ሠላምና ዕድገት የማዕዘን ድንጋይ ነው”

\- ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-የአፍሪካ ሀገራት ትብብርና አጋርነት ለአሕጉሪቱ ሠላምና ዕድገት ወሳኝ ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ ገለጹ፡፡

የአፍሪካ አሕጉራዊ የሠላም ኮንፈረንስ "የበለፀገችና ሠላማዊ አፍሪካን እንገንባ" በሚል መሪ ሀሳብ በአዲስ አበባ ትላንት መካሄድ ጀምሯል።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ በመክፈቻ ንግግራቸው እንደገለጹት፣ የአፍሪካ ሀገራት ትብብርና አጋርነት ለአሕጉሪቱ ሠላምና ዕድገት ወሳኝ ነው፡፡

ለአፍሪካ ሠላምና ብልፅግና የአፍሪካ አሕጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና ተግባራዊ መሆን ወሳኝ መሆኑን በመግለጽ፣ ግንኙነቶችን በማጎልበት የበለጠ የተቀናጀ፣ ጠንካራና የበለፀገ አሕጉር ለመፍጠር የሚደረጉ ጥረቶች መጠናከር እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

አፍሪካ ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ በንግድና በቴክኖሎጂ ላይ ያተኮሩ ጠንካራ አሠራሮችን ልትከተል ይገባል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ አፍሪካ ያላትን አቅም ተጠቅማ ወደፊት መራመድ አለባት ብለዋል።

“የአፍሪካ ሀገራት ትብብርና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፦ ዳኜ አበራ



ሂሩት ገብረሥላሴ

# አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከኮሚሽኑ ጋር በትብብር እየሠሩ ነው

**ኢያሱ መሰለ**

አዲስ አበባ፡- አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር በትብብር በመሥራት ላይ እንደሚገኙ የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አስታወቀ። ኮሚሽኑ አሁንም ለቀሩት ለተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የትጥቅ ትግል ለሚያደርጉ አካላት ሁሉ ጥሪ አቅርቧል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን

አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ልዩ የምርመራ ዘገባ

በሃገራችን ገና በጅምሩ በብዙ ውስብስብ ችግሮች እየተፈተነ ለዜጎች የእሮሮ ምንጭ በሆነው የሪል ስቴት ንግድ ዙሪያ ያዘጋጀነውን ልዩ የምርመራ ዘገባ በገጽ 8 ይመልከቱ

# ለመጪው ትውልድ የተሻለች አፍሪካን ለመፍጠር አሕጉራዊ አጋርነትን ማጠናከር ወሳኝ ጉዳይ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ለመጪው ትውልድ የተሻለች አፍሪካን ለመፍጠር አሕጉራዊ አጋርነትን ማጠናከር ወሳኝ ነው ሲሉ የሠላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዱዓለም ገለጹ፡፡

የአፍሪካ አሕጉራዊ የሠላም ኮንፈረንስ "የበለፀገችና ሠላማዊ አፍሪካን እንገንባ" በሚል መሪ ሀሳብ በአዲስ አበባ ትላንት መካሄድ ጀምሯል።

የሠላም ሚኒስትር ብናልፍ አንዱዓለም በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፣ ለመጪው ትውልድ የተሻለች አፍሪካን ለመፍጠር አሕጉራዊ አጋርነትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

ሠላም በድንበር የማይገደብና የሁሉም መሆኑን መገንዘብ እንደሚያስፈልግ የገለጹት ሚኒስትሩ፤ እኛ አፍሪካውያን በፓን አፍሪካኒዝም መንፈስ ለሠላም እጅ ለእጅ ተያይዘን ልንሠራ ይገባል ብለዋል፡፡

የአፍሪካውያንን ብዝኃነት በመጠቀም ጠንካራ አሕጉራዊ አንድነት መፍጠር እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፣ ለችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔዎች በማበጀት ወደ ዘላቂ ሠላም የሚያደርሰውን መንገድ መቀየስና መጓዝ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡



አቶ ብናልፍ አንዱዓለም

ኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር፤ የሽግግር ፍትሕንና የቀድሞ ተዋጊዎችን መልሶ በማቋቋም ዘላቂ ሠላምን ለማረጋገጥ እየሠራች ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ኢትዮጵያ በሀገራዊ አንድነትና ለኅብረ ብሔራዊ ትርክትን ለመገንባት እየሠራች ይገኛል ብለዋል፡፡

የሰሜኑን ጦርነት በሠላም ለመቋጨትና የፕሪቶሪያው

ለመጪው ትውልድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ለሀገራዊ መግባባት

**ታደሠ ብናልፈው**

በኢትዮጵያ የሚገኙ ከ80 በላይ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በባሕላዊ አለባበስ ደምቀው፤ በተለያዩ ጌጦች አጊጠው፤ በባሕላዊ ሙዚቃቸውና ውዝዋዜያቸው እያዜሙና እያሳዩ፤ በየቋንቋቸው እየተናገሩ፣ እየተግባቡ በጉራማይሌ ውብት ኅዳር 29 ቀን ያከብራሉ፡፡

የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን የብዙኃን እኩልነት ማለትም የቋንቋ፤ የባሕል፤ የኃይማኖት እኩልነትን ያረጋገጠው እና የሀገር ሀብትን በፍትሕዊነት የመጠቀም መብትን ያጎናጸፈውን ኅዳር 29 ቀን በየዓመቱ ያከብራሉ።

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ኅዳር 29 ቀን ሲያከብሩ አለመግባባትን በሚፈታ

የብሔሮች ብሔረሰቦችና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# በክልሉ ኢንዱስትሪዎች የሚያጋጥማቸውን የመሠረተ ልማት ክፍተቶች የማስተካከል ሥራ እየተሠራ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል ኢንዱስትሪዎች የሚያጋጥማቸውን የመሠረተ ልማትና የፋይናንስ ክፍተቶች የማስተካከል ሥራ እየተሠራ መሆኑን የክልሉ ከተሞችና መሠረተ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የክልሉ ከፍተኛ አመራር አባላት በወረታ ከተማ የሚገኙ የኢንዱስትሪ መንደሮችን ጎብኝተዋል።

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የከተሞች ልማት ዘርፍ አስተባባሪና የከተሞች እና መሠረተ ልማት ቢሮ ኃላፊ አሕመዲን መሐመድ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የግብርና ምርትን ከኢንዱስትሪዎች ጋር የማስተሳሰር ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው።

ለዚህም በወረታ ከተማ ለኢንዱስትሪው በተሰጠው ትኩረት የተገነባና በግንባታ ላይ የሚገኝ የኢንዱስትሪ መንደርን መመልከታቸውን ገልጸዋል።

ኢንዱስትሪዎቹ ከግብዓት አቅርቦት ችግር ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለማስተካከል በከተማ አስተዳደሩ እየተከናወኑ የሚገኙ ሥራዎች መኖራቸውን አመልክተዋል።

የክልሉ ኢንዱስትሪዎች የሚያጋጥማቸውን የመሠረተ ልማትና የፋይናንስ ችግሮች መፍታት የሚያስችሉ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑንም ተናግረዋል።

በተለይም የ"ኢትዮጵያ ታምርት" ንቅናቄ ዘርፈ ብዙ እያሳየ የመጣው ለውጥ ተጠናክሮ መቀጠሉን አስረድተዋል።

ከወረታ ከተማ በቅርብ ርቀት የወረታ ደረቅ ወደብ የሚገኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞም በአካባቢው የሚመረተውን የግብርና ምርት ከኢንዱስትሪዎች ጋር የማስተሳሰሩ ተግባር እንደሚጠናከር ገልጸዋል።

የወረታ ከተማ አስተዳደር ተቀዳሚ ምክትል ከንቲባ አቶ ጌትነት ፈረደ በበኩላቸው፤ በኢንዱስትሪ መንደሩ በመጀመሪያው ምዕራፍ ባለሀብቶች ግንባታ አጠናቀው ማሽን ተከላ ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በግንባታ ላይ የሚገኙት ኢንዱስትሪዎች በፍጥነት አጠናቀው ወደ ማምረት እንዲሸጋገሩም አስተዳደሩ ድጋፍና ክትትል እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ባለሀብቶቹ የሚያቀርቧቸውን የመንገድና ሌሎች የመሠረተ ልማት ችግሮች ደረጃ በደረጃ እየተፈቱ እንደሆነም ጠቁመዋል።

ከተማዋ ካላት ብዝኃ ፀጋ ጋር ተያይዞ 22 ባለሀብቶች ቦታ ተረክበው በዱቄትና በዓሣ ማቀነባበር፤ በቺፑድ ማምረትና ሌሎች የሥራ ዘርፎች ወደ ሥራ ለመግባት እየተንቀሳቀሱ እንደሚገኙ አስረድተዋል።

በአካባቢው ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ የሩዝ፣ የስንዴና የዓሣ ምርት በስፋት የሚገኝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በእነዚህ ዘርፎች መሰማራት ፍላጎት ላላቸው ባለሀብቶች 114 ሄክታር መሬት መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

በጉብኝቱ የክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ፋንቱ ተስፋዬ፤ የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር አብዱ ሁሴን (ዶ/ር)፣ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የማኅበራዊ ዘርፍ አስተባባሪና የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ሙሉነሽ ደሴ (ዶ/ር)ን ጨምሮ ሌሎች አመራር አባላት መሳተፋቸውን ኢዜአ ዘግቧል።




## የኢትዮጵያ አየር መንገድን በአባልነት ያቀፈው "ስታር አላያንስ" ምርጥ የአየር መንገዶች ኅብረት በሚል ተሸለመ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ 25 የዓለማችን ግዙፍ አየር መንገዶች ኅብረት የሆነው "ስታር አላያንስ" የ2024 ዎርልድ ትራቭል አዋርድ ላይ ምርጥ የአየር መንገዶች ኅብረት በሚል ተሸልሟል፡፡ "ስታር አላያንስ" ውድድሩን ሲያሸንፍ ይህ ለ5ኛ ተከታታይ ዓመት መሆኑ ተጠቅሷል፡፡

የዘንድሮው የሽልማት አሰጣጥ መርሐ ግብር በፖርቹጋል ማዲዬራ መካሄዱንም ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ፣ በቶጎ አየር መንገድ አስካይ ኤር ዌይስ፣ በማላዊ ማላዊ ኤርዌይስ፤ በዛምቢያ ዛምቢያ ኤር ዌይስን በማቋቋም ድርሻ ይዞ እየሠራ መሆኑ ይታወቃል፡፡

## በኅዳር ወር የመጨረሻዎቹ ቀናት ከቀላል እስከ መካከለኛ ዝናብ ይኖራል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በኅዳር ወር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ ዝናብ እንደሚኖር የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው ሪፖርት፤ በኅዳር ወር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡

በኅዳር ወር መጨረሻ አስር ቀናት ወይም በፈረንጆቹ የዲሴምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እንዳሉም ጠቁሟል፡፡

በተጨማሪም በመካከለኛው፣ በምሥራቅ፤ በሰሜን ምሥራቅ፣ በሰሜንና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንደሚኖር ሪፖርቱ አመላክቷል፡፡

በሚቀጥሉት ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀጣይነት እንደሚኖራቸው ያመላከተው ኢንስቲትዩቱ፤ በፀሐይ ኃይል ታግዞ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይዘንባል፡፡

እንደ ኢንስቲትዩቱ ገለጻ፤ በሚቀጥሉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ኦሮሚያ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማ፣ ሱማሌ፣ ሐረሪ ክልሎችና ድሬዳዋ ዞኖች ላይ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአማራ፣ ትግራይ፣ አፋር፣ ኦሮሚያ፣ አዲስ አበባ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ ሐረሪ ክልሎችና ድሬዳዋ ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ሊኖር እንደሚችል አኃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ ብሏል፡፡

በሰሜን፣ በመካከለኛውና በምሥራቅ የሀገሪቱ የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ በሪፖርቱ አመላክቷል፡፡

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA
የዜጎች ጤና ለሃገር ብልጽግና!
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!

# በከተሞች ያለው የኤች አይ ቪ ስርጭት ከገጠር ሰባት እጥፍ እንደሚልቅ ተገለፀ

**ነፃነት ዓለሙ**

አዲስ አበባ፡-በከተሞች ያለው የኤች አይቪ የስርጭት መጠን ከገጠር አካባቢዎች በሰባት እጥፍ እንደሚልቅ በጤና ሚኒስቴር የኤች አይቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈፃሚ ዘርፍ ያገኘነው መረጃ ጠቁሟል፡፡

እንደ ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ገለፃ የኤች አይቪ ኤድስ የስርጭት ምጣኔ በገጠር 0 ነጥብ 4 በመቶ አካባቢ ሲሆን በከተሞች ግን ወደ ሦስት በመቶ ይጠጋል፡፡

ዓለም ላይ 39 ነጥብ 9 ሚሊዮን ሕዝብ ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖር ይገመታል የሚለው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መረጃ፤ በየዓመቱ ደግሞ አንድ ነጥብ 3 ሚሊዮን ሕዝብ ለቫይረሱ ተጋላጭ እንደሆነና 630ሺህ ሰዎች ደግሞ በቫይረሱ ምክንያት እንደሚሞቱ ያብራራል፡፡

በኢትዮጵያ ከ600ሺህ በላይ ሰዎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩም መረጃው አመልክቶ፤ በዓመት ከሰባት ሺህ በላይ ሰዎች ለቫይረሱ ተጋላጭ እንደሚሆኑ እና በየዓመቱ ከ10 ሺህ በላይ ሰዎች በቫይረሱ ምክንያት ሕይወታቸውን እንደሚያጡ ገልጿል፡፡

እንደሀገር የስርጭት መጠኑ ከአንድ በመቶ በታች በመሆኑ ከወረርሽኝነቱ ወጥተናል ያለው ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ፤ የሀገሪቱን አካባቢዎች የስርጭት መጠን ሲታይ አሁንም ወረርሽኝ ውስጥ ነን የሚያስብል መሆኑንም ጠቁሟል፡፡ ሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከአንድ በመቶ በታች የሆነ ውጤት ሲመዘገብ ውጤታማ ነን ማለት እንደሚቻልም አመላክቷል፡፡

አዲስ ተጋላጮችን እንዲሁም በቫይረሱ ምክንያት የሚከሰት ሞትን ለመቀነስ ታቅዶ ሲሠራ እንደቆየ የሚያሳየው መረጃው፤ አዲስ ተጋላጮችን ከመቀነስ አኳያ የዕቅዱን 70 በመቶ ማሳካቱን አስታውቋል፡፡

በቫይረሱ ምክንያት የሚከሰት ሞትን ከመቀነስ አኳያ ግን አርባ ዘጠኝ በመቶ ብቻ ማሳካቱን የገለፀው ሚኒስቴሩ ብዙ ቀሪ ሥራዎች እንዳሉ ጠቁሟል፡፡

በተለይ በከተሞች ለሚታየው የስርጭት መጠን እንደ መፍትሔ ሦስት ቁልፍ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተብለው የተለዩ አካላት ላይ መሥራት እንደሆነ ያመላከተው ሚኒስቴሩ፣ እነሱም በወሲብ ንግድ የሚተዳደሩ ሴቶች፣ እስረኞች እና በመርፌ የሚወሰዱ ሱስ አስያዥ መድኃኒቶችን የሚጠቀሙ ሰዎች መሆናቸውን ጠቅሷል፡፡

የምርመራ አገልግሎቱን ለኤች አይ ቪ ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮረ ማድረግ፣ የአቅም ግንባታና የክትትል ሥራን ማጠናከር፣ ግንዛቤና ቅድመ መከላከል ላይ መሥራትም የመፍትሔ አቅጣጫዎች ተብለው በሚኒስቴሩ ከተጠቀሱት ጥቂቶቹ መሆናቸው ታውቋል፡፡

# ‹‹የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ከብሔራዊ ጥቅም ጋር በፅኑ የተሳሰረ ነው››

**- አምባሳደር ዲና ሙፍቲ**
**የውጭ ግንኙነት እና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል**

**ምሕረት ሞገስ**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ከብሔራዊ ጥቅም ጋር በፅኑ የተሳሰረ መሆኑን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ተናገሩ፡፡ የባሕር በር ለማግኘት የሚደረገው ጥረትም ሰጥቶ በመቀበል እንዲሁም ከሚመለከታቸው ጋር አብሮ በመሥራት ብቻ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በተለይ ለአዲስ ዘመን እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በከፍተኛ የኢኮኖሚ ግስጋሴ ውስጥ የምትገኝ ሀገር በመሆኗ በየጊዜው የወጪ እና የገቢ ንግዷ እያደገ ይገኛል፡፡ በዚህ የተነሳም በአንድ ወደብ ብቻ መጠቀም የሚቻልበት ጊዜ አልፏል፡፡ ላለፉት 30 ዓመታት በላይ ስትጠቀምበት ከነበረው ጅቡቲ ወደብ በተጨማሪ ሌሎች ወደቦችን መጠቀም የግድ የሚልበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡

ሌሎች ወደቦችን ለማግኘት ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርማለች፡፡ በሂደት ስምምነቱ ይተገበራል፡፡ በዚህ ስምምነት ደግሞ ሶማሌ ላንድ እና ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ የአካባቢው ሀገሮችም ተጠቃሚ መሆናቸው አይቀርም ብለዋል፡፡

የባሕር በር ዕድልን ለማስፋት ከሶማሌ ላንድ ጋር ብቻ ሳይሆን ሌሎች የባሕር በር ካላቸው የአካባቢው ሀገሮች ጋር አብሮ በመሥራት፣ በመገናኘት እና በመጠቃቀም የባሕር በር ሊገኝ የሚችልበት ሁኔታ ላይም እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች ውስጥም ወደብ የማግኘት መብት እንዳላት የተደነገገ መሆኑና የባሕር በር ማግኘት ሕጋዊ መብቷ መሆኑን አስታውሰው፤ ይህንን መብቷን ለማረጋገጥ የምትጥረው በሠላማዊ መንገድ ብቻ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

በተያያዘም ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሠላም ጥበቃ በዓለም አቀፍ ደረጃ በኮንጎ፣ በላይቤሪያ በብሩንዲ በሩዋንዳ ከፍተኛ ሥራ ስትሠራ የነበረች ሀገር መሆኗን ያስታወሱት ቃል አቀባዩ፤ የኢትዮጵያን ሠላም አስከባሪነት ምዕራባውያኑም የሚያውቁት ጉዳይ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ በሶማሊያም ሆነ በሌሎች ሀገራት ኢትዮጵያ የምታደርገው የሠላም ማስከበር እንቅስቃሴ ሲደነቅ መቆየቱን ተናግረዋል፡፡

ለምሥራቅ አፍሪካ ሠላም መስፈን ኢትዮጵያ ያላት አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ አልሸባብን በመዋጋት እና በማዳከም ከፍተኛ ሚና መጫወቷ እንደተመሰከረላት አመላክተዋል፡፡ ኢትዮጵያ የሌለችበት የሠላም ማስከበር ሂደት አዋጭ እንደማይሆንም ጠቁመዋል፡፡

አምባሳደር ዲና እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ የሶማሊያን ሠላም የምትፈልገው እንደራሷ ሠላም ስለምታየው ነው፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ እንደምታምነው፤ የጎረቤት ሀገሮች ሠላም የኢትዮጵያም ሠላም ነው፡፡ እነርሱ ችግር ላይ ከወደቁ ሀገሪቱም ችግር ላይ ትወድቃለች፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በኢትዮጵያ ሠላም ከሌለ እና ሀገሪቱ ችግር ላይ ከወደቀች ሶማሊያን ጨምሮ ሌሎች የጎረቤት ሀገሮችም በተመሳሳይ መልኩ ችግር ላይ ይወድቃሉ፡፡ ከዚህ አኳያ የጋራ ጥቅም በመኖሩ የኢትዮጵያ በቀጣናው የሚኖራት የሠላም ሚና ወደ ፊትም ይቀጥላል ብለዋል፡፡

# በግብርናው ዘርፍ በአጭር ጊዜ አስደናቂ ለውጦች እየተመዘገቡ ናቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በግብርናው ዘርፍ ያሉትን እምቅ አቅሞች በመለየት ወደ ተግባር በመግባት በአጭር ጊዜ አስደናቂ ለውጦች መመዝገባቸውን የኢፌዴሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ፡፡ አገልግሎቱ ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማረጋገጥ በመንግሥት ተቀርፀ ሥራ ላይ የዋሉ የመንግሥት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች በተጨባጭ ተግባራዊ እየሆኑ ነው ብሏል፡፡

በመንግሥት ከሙኒኬሽን አገልግሎት አስተባባሪነት ከተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የተውጣጡ የጋዘጠኞች ቡድን በኦሮሚያ ክልል አርሲ እና ባሌ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች በተጨባጭ ሁኔታ መሬት ላይ ተግባራዊ እየሆነ ያለውን የግብርና ሥራዎችን ምልከታ አድርጓል፡፡

በባሌና አርሲ ዞኖች ምልከታ በተደረገባቸው የተለያዩ ወረዳዎች በሁሉም ዘርፍ የአርሶ አደሩን ሕይወት ለመለወጥ በመንግሥት ተቀርፆ ተግባራዊ እየሆነ ካለው አዳዲስ መርሐ ግብሮች (ኢኒሼቲቮች) መካከል የግብርና ልማት ሥራዎች አንዱ ሲሆን፣ እየተከናወኑ ባሉ ተግባራት ተጨባጭ ለውጦች መምጣታቸውን መመልከት ተችሏል፡፡

በክላስተር የለማው የስንዴ ምርት፣ በዘመናዊ የእንስሳት እርባታ፣ ዘመናዊ ቀፎን ተጠቅሞ በንብ እርባታ ላይ የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ወጣቶች፣ እንዲሁም በቤተሰብ ደረጃ በሌማት ትሩፋት ሥራ ኑሯቸውን እየቀየሩ መሆኑን መመልከተ መቻሉን አገልግሎቱ አስታውቋል፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ከበደ ዴሲሳ በሚዲያ ቅኝቱ ወቅት በሰጡት ማብራሪያ ግብርናን በተመለከተ የመንግሥት ዋናው ትኩረት የምግብ ሉዓላዊነትን ማረጋገጥና በቂ ምርት አምርተው ለገበያ ማቅረብ ሲሆን እቅዱ በተጨባጭ ተግባራዊ መሆኑን፣ እንዲሁም ሀገሪቱ ያላትን እምቅ አቅሞች በመለየት ወደ ተግባር በመግባት በአጭር ጊዜ አስደናቂ ለውጦች መመዝገባቸውን አንስተዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአርሶ እና አርብቶ አደሩን የሕይወት ዘይቤ እንዲቀየርና ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ግብርና ከባሕላዊ ዘዴ ወደ ዘመናዊነት እንዲሸጋገር በማድረግ ላይ የተከናወኑ ሥራዎች አበረታች ውጤቶችን እያስመዘገቡ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

ይህንን ተግባር ለማሳካትም መንግሥት ለአርሶ አደሩ ከሙያዊ እገዛ ጀምሮ እስከ ሜካናይዜሽንና የግብርና ግብዓት አቅርቦት ትራክተር፤ ኮምባይነርና የሌሎች ግብዓቶች አቅርቦትን በማመቻቸት ዘርፈ ብዙ ድጋፎች መደረጋቸውን ገልፀዋል፡፡

ይህንን ተከትሎም መንግሥት በአርሶ አደር ማሳ ላይ የሚመረት ምርት በብዛት፤ ጥራትና ፍጥነት እንዲመረት የመንግሥት ቁልፍ ተግባር በመሆኑ በክላስተር፤ ጥምር ግብርና እና ሌማት ትሩፋት ላይ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች አመላካች መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለፃ እንደ ሀገር መንግሥት የኢኮኖሚው ተግባር ውጤታማ እንዲሆን አራቱ የኢኮኖሚ ግቦች ብሎ የለያቸው ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፤ ኤክስፖርትን ማሳደግ፤ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እና የሥራ ዕድል ፈጠራ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በባሌ እና አርሲ ዞን በተጨባጭ ሁኔታ ሁለንተናዊ የቤተሰብ ብልፅግናን ለማረጋገጥ ተግባራዊ እየሆኑ ያሉ አዲስ ኢኒሼቲቭ የሆነው የግብርና ዘርፍ ስንዴን በክላስተር ማምረት፤ በቢራ ገብስ፤ በሌማት ትሩፋት እና ሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች ትልቅ ለውጥ ማምጣታቸውና ለሁሉም ልማት ሥራዎች ወሳኝ የሆነ በዞኖቹ ሠላም በመረጋገጡ መሆኑን ተናግረዋል፡፡



ፍሬሕይወት ለገሰ



ወይዘሮ መቅደስ ተክሉ



ወይዘሮ እቴነሽ ለገሠ

# የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች..

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን በሚገነባና በሚያፀና መልኩ ነው፡፡ የዘንድሮው 19ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል "ሀገራዊ መግባባት ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሀሳብ የፊታችን ኅዳር 29 በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በአርባ ምንጭ ከተማ ይከበራል፡፡

ቀኑ ሁሉም የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነታቸው እንዲከበርና በቀጣይ ለፍትሕ፣ ነፃነትና ለዲሞክራሲ ሥርዓት መከበርና መረጋገጥ በጋራ ጠንክረው እንዲሠሩ በጋራ የሚነሱበትን መሠረት የጣለ ነው፡፡ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቶች፣ ትስስርና አንድነት የሚያጠናክሩ እንዲሁም የብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቱባ ባሕሎቻቸው፤ እሴቶቻቸው የሚያስተዋውቁበት ዕድልንም የፈጠረ ነው፡፡

የቦሌ ክፍለ ከተማ ሴቶች ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ቡድን መሪ ፍሬሕይወት ለገሠ ለኢፕድ በሰጡት አስተያየት፤ የኅዳር 29 መከበር የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ሀገራዊ አንድነትንና መግባባት የሚያጸና ነው፤ እንደሀገር እያጋጠሙ ያሉ አለመግባባቶችን በመቻቻልና በመከባበር መፍትሔ እንዲያገኙና ሕዝቦች በሠላም እንዲኖሩ የሚያደርግ ነው ይላሉ፡፡

በየዓመቱ የሚከበረው ኅዳር 29 የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በኢትዮጵያ የሚኖር ሁሉም ዜጋ በዘር፤ በሃይማኖት፣ በብሔር ሳይለያይ ሰው በመሆኑ ተከባብሮ በእኩልነት እንዲኖር የሚያደርግ ነው፤ ዜጎች በእኩልነት መኖራቸውም ሠላምና አንድነትን ያስቀጥላል ሲሉ አስተያየታቸው ሰጥተውናል፡፡

ኅዳር 29 ቀን የሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል ልዩነታችን ድምቀታችን፤ ለአንድነታችን ውበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፤ በዘር፣ በሃይማኖትና በቋንቋ ሳንለያይ ተባብረን በአንድነት እንድንኖር የሚያደርግ ነው፤ ይህም ሀገራዊ መግባባትን የሚያፀና ነው ሲሉ ያብራራሉ፡፡

በሀገራዊ መግባባት ላይ የሴቶች ሚና ትልቅ ነው፤ ሴቶች በልማት፤ በበጎ ፍቃድና በሠላም ግንባታ ላይ እየተጫወቱት ያለው ፋይዳ ትልቅ ነው፡፡ በልዩነት ጉራማይሌ ውበት፤ በጉራማይሌ ውበት ድምቀት፤ በልዩነት አንድነት የሚስተዋልበት የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ኅዳር 29 መከበሩ ኢትዮጵያዊነትን ያስተምራል፤ ይሰብካልም ነው ያሉት፡፡

የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ሴቶች ማኅበር ሰብሳቢ ወይዘሮ መቅደስ ተክሉ በበኩላቸው፤ ኅዳር 29 የብሔር ብሔረሰቦች ቀን መከበሩ ሠላምና አንድነትን የሚያረጋግጥ፤ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን የሚያዳብር ነው ብለዋል፡፡

ልዩነታችን የሚያጣላንና የሚያጋጨን ሳይሆን ውበታችን ነው፤ ውበታችን የሆነውን ልዩነታችንን በማቻቻል፤ በአንድነት እንድንኖር እሴቶቻችን፤ ባሕላችን መከበር አለባቸው፤ ጠብና ንትርክን ትተን በሠላምና በአንድነት መኖር አለብን ይላሉ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ደስ የሚልና የሚያኮራ ማንነት አላቸው፤ በሚያኮራ ማንነት በሠላምና በፍቅር መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች ውቅር ናት፤ አንዱ የአንዱን ባሕል፤ ቋንቋ፤ ሃይማኖት አክብሮ በፍቅርና በአንድነት መኖር አለበት ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

በመመካከር፤ በመከባበር አብሮ መኖርን ከአባቶቻችን ተምረናል፤ አሁን ግን አባቶቻችን ያስተማሩንን አክብሮት ጥለን ብሔርን አንስተናል፤ ያነሳነው ጽንፍ የወጣ ብሔርተኝነት አይጠቅመንም፤ እንደ ሰው ተከባብረን፤ ያለንን አቃፊነት፤ ሰብሳቢነት በማስቀጠል በፍቅርና በሠላም መኖር ይገባናል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ብሔር የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን በተፈጥሮ የሚሰጥ ነው፤ በተፈጥሮ በተሰጠ ነገር መጋጨት አስፈላጊ አይደለም፤ በሰውነታችን ተባብረን መኖር ነው አስፈላጊው ነገር ይላሉ፡፡

ኅዳር 29 የሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ያሉብንን ችግሮች ቀርፎ አንድነትን የሚያስተምር ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የፊታችን ኅዳር 29 ቀን የሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦች በዓል አንድነትን ለማምጣት ትልቅ አስተዋፅዖ አለው ሲሉ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ነዋሪ ወይዘሮ እቴነሽ ለገሠ ይናገራሉ፡፡

ኅዳር 29 ቀን የሚከበረው የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ኅብረ ብሔራዊነትን፤ አንድነትንና መቻቻልን የሚያስተምር በመሆኑ ሀገራዊ መግባባትን የሚያመጣ ነው ይላሉ፡፡

‹‹እኔ አማራም ኦሮሞም ነኝ፤ ከሁለቱም ብሔሮች ነው የተወለድኩት፤ ከሁሉም ብሔሮች መፈጠሬን ምርጫዬ ሳይሆን በተፈጥሮ ያገኘሁት ነው፤ በተፈጥሮ የተገኘ ብሔር ሊያጣላም ሆነ ሊያጋጭ አይችልም፤ በሰውነት ተከባብሮና ተዋዶ መኖር ዘላቂ ሠላም የሚያስገኘው›› ሲሉ ያብራራሉ፡፡

ችግሮችን በውይይትና በሠላም በመፍታት፣ በፍቅርና አብሮነት መኖር ያስፈልጋል፤ ወጣቱ መንግሥትና ራሱ በፈጠረው የሥራ ዕድል በመሰማራት ራሱንና ሀገሩን ማሳደግ እንዳለበት አመልክተዋል፡፡

ኅዳር 29 ቀን የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን የድምቀታቸው፤ የውበታቸው፤ የአብሮነታቸው መገለጫ ነው፡፡ በዓሉ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት የፀደቀበትን ኅዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም ለመዘከር የሚከበር በዓል ነው። የበዓሉ መከበር ዋነኛ ፋይዳ በአገራችን ሕገ መንግሥትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ኅብረተሰቡ የተሻለ ግንዛቤ እንዲያገኝ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ያለመ ነው፡፡

# አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት ገብረሥላሴ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር በነበራቸው ቆይታ አብዛኞዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ጋር በትብብር እየሠሩ እንደሚገኙና ጥቂቶች ግን ወደ ኮሚሽኑ መቅረብ እንዳልፈለጉ ገልጸዋል፡፡

ኮሚሽኑ ሥራ በጀመረ ሰሞን ጥሪውን ተቀብለው በጋራ ለመሥራት ፍላጎት ያሳዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አነስተኛ ነበሩ ያሉት ኮሚሽነሯ፤ በአሁኑ ጊዜ አብዛኞዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከኮሚሽኑ ጋር በትብብር እየሠሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ተሳትፎ ሊያድግ የቻለው የኮሚሽኑን ገለልተኝነትና አካታችነት እየተረዱ በመምጣታቸው እንደሆነም የጠቀሱት ኮሚሽነሯ፤ ራሳቸውን ያገለሉት ጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎችም ቀረብ ብለው ሂደቱን ቢመለከቱ፣ አካሄዱን ቢፈትሹና ወደ መጨረሻው ውሳኔ ላይ ቢደርሱ እንደሚሻል መክረዋል፤

ሠላማዊ የፖለቲካ ትግል ማድረግን ዓላማው አድርጎ ለተቋቋመ የፖለቲካ ፓርቲ ሀገራዊ የምክክር መድረኩ ጥሩ አጋጣሚ ነው ያሉት ኮሚሽነር ሂሩት፤ ዕድሉን አለመጠቀም በራሱ የሚያስቆጭ ይሆናል ነው ያሉት፡፡

ኮሚሽኑ ለፖለቲካ ፓርቲዎቹ በተደጋጋሚ ጊዜ ጥሪ ሲያቀርብ እንደነበረ እና በአካልም እንዳነጋገራቸው ገልጸው፤ አሁንም በሀገራዊ ምክክሩ መሳተፍ ለሚፈልጉ ሁሉ ኮሚሽኑ በሩን ክፍት አድርጎ እየጠበቃቸው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የትጥቅ ትግል ውስጥ የገቡ አካላት ተወካዮችም ምንም አይነት የስጋትና የደኅንነት ጥርጣሬ ሳይኖራቸው መጥተው በሀገራዊ ምክክሩ ላይ እንዲሳተፉ ኮሚሽኑ ጥሪ አቅርቧል፡፡

የደኅንነት ስጋት እንዳይፈጠርባቸው ዋስትና የሚሰጡና ሁኔታውን የሚያመቻቹ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መኖራቸውን ጠቁመው፤ መንግሥትም በጉዳዩ ላይ ፍቃደኝነቱን እንደገለጸ ተናግረዋል፡፡

‹‹አለመግባባት በጦርነት አይፈታም፤ ችግሮችን በውይይት መፍታት እየቻልን ብዙ ምሑራንና ወጣቶችን ያጣንባቸው መጥፎ አጋጣሚዎች ሊያስቆጩን ይገባል›› ያሉት ኮሚሽነር ሂሩት፤ በከፍተኛ ልፋትና ድካም ተምረው ለጥሩ ውጤት የበቁ ብርቅና ውድ ዜጎች ተነጋግረን መፍታት ስንችል ግጭት ውስጥ መግባት ለሀገርም የከፋ ጉዳት ያስከትላል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

እንደ ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት ገለጻ፤ ወደ ትጥቅ ትግል አስገብቶናል፤ እንዳንግባባ አድርጎናል የሚባሉ ጉዳዮች ካሉ ቁጭ ብለው በመመካከር ሊፈቱ የማይችሉበት ምንም አይነት ምክንያት የለም፡፡

ኢትዮጵያውያን ትልቁ ችግራችን አንዱ አካል ሲሠራ ሌሎቻችን ተመልካች፣ ታዛቢ እና ተቺ መሆናችን ነው ያሉት ምክትል ዋና ኮሚሽነሯ፤ ይህ አስተሳሰባችን ወደ ችግር እየከተተን መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡ እውነትን መፈለግ፣ የሌላውን የማኅበረሰብ ክፍል ወይም የሀገራችንን ዜጋ ቁስል ማዳመጥ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት እና የሲቪክ ማኅበራትም የሩቅ ተመልካች ከመሆን ይልቅ ቀረብ ብለው የሚጠበቅባቸውን እንዲሠሩ ኮሚሽነሯ አሳስበው፤ ሁሉም ሚናውን ሲወጣ ሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማ የማይሆንበት ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖርም ሲሉ ገልጸዋል፡፡

# "የአፍሪካ ሀገራት ትብብርና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አፍሪካ ለሚመጡ የሠላምና የብልፅግና ተግዳሮቶችና ዕድሎች እራሷን ማዘጋጀት እንዳለባት ጠቅሰው፣ የተወሳሰቡ የሠላም ግንባታ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ተቋማትን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአሕጉሪቱ ዘላቂ ሠላምን በማረጋገጥ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ማስቀጠል አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ስጋትን መቅረፍ ዘላቂ መፍትሔዎች መሆናቸውን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ችግር በአፍሪካዊ መፍትሔ መስጠት ይገባል የሚል ጽኑ አቋም አላት ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ የፕሪቶሪያው ስምምነት የአፍሪካውያንን ችግር በአፍሪካውያን መፈታት አለበት የሚለውን አቋም በተግባር ያሳየ ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በማድረግ በቀጣናው ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ገንቢ ሚና እየተወጣች መሆኑን ጠቅሰው፣ በአፍሪካ ሰላምና ደኅንነትን ለማረጋገጥ ምቹ ሁኔታን እየፈጠረች መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ሠላምና ደኅንነት እንዲረጋገጥ ምቹ ሁኔታን እየፈጠረች ያለች ሀገር ናት ሲሉ ፕሬዚዳንት ታዬ ተናግረዋል፡፡

የሠላም ኮንፈረንሱ ቀጣናዊ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር እንዲፈጠርና እንዲስፋፋ የሚያደርግ፤ መሆኑን በመግለጽ የአፍሪካ ሠላምና ልማት የሚያበረታቱ ሀሳቦችን ለማፍለቅና ሠላምና ብልፅግናን ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት አጋዥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በጉባኤው ላይ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር፣ የሠላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዱዓለምን ጨምሮ ሚኒስትሮች፣ ርዕሳነ መስተዳድሮች፣ የተለያዩ ሀገራት አምባሳደሮች፣ የሃይማኖት አባቶችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል፡፡

# ለመጪው ትውልድ የተሻለች አፍሪካን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሠላም ስምምነት እውን እንዲሆን ጥረት መደረጉን ጠቅሰው፣ በስምምነቱ መሠረት ዘላቂ ሠላም ለማረጋገጥ በመልሶ ግንባታና ማቋቋም ሥራዎች ተጨባጭ ውጤት መመዝገቡን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የተለያዩ እምነቶችና አመለካከቶች የሚንፀባረቁባት ሀገር መሆኗን በመግለጽ፣ በሀገሪቱ የወል ትርክት ተገንብቶ ኅብረ ብሔራዊነት እንዲሰፍን ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ እያካሄደች ያለችው የሽግግር ፍትሕ፣ ሀገራዊ ምክክርና የብሔራዊ የተሐድሶ ለሠላም ያላትን ቁርጠኝነት ማሳያዎች መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ በአሕጉሪቱ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት በቁርጠኝነት እየሠራች ትገኛለች፡፡ የአፍሪካ ሀገራት ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔዎችን ተግባራዊ በማድረግ በትብብር ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብርን ተግባራዊ እያደረገች መሆኑን ገልጸው፤ ይህም አካባቢ ጥበቃ ከሠላም ግንባታ ጥረቶች ጋር የሚመጋገብ መሆኑን ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለዘላቂ ሠላም ዓለም አቀፍ ትብብር!

በዓለማችን ግጭቶች እና ጦርነቶች ከዕለት ዕለት እየተባባሱ በመምጣታቸው የሠላም ጉዳይ ከመቼውም ይልቅ ዓለም አቀፍ አጀንዳ ሆኗል። ሀገራት፣ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ የሀገራት መሪዎች፣ ተደማጭነት ያላቸው ግለሰቦች.. ወዘተ ሠላምን ዋነኛ አጀንዳ አድርገው ሲንቀሳቀሱ እና ዓለም ለሠላም ተገቢውን ትኩረት መስጠት እንዳለባት አበክረው ሲያስገነዝቡ ይስተዋላል ።

በርግጥም ዓለማችን አሁን ላይ በብዙ መልኩ እያጋጠማት ካለው የሠላም እጦት፤ ከችግሩ ጋር በተያያዘ እየከፈለች ካለው ያልተገባ ዋጋ አኳያ፤ የሠላም ጉዳይ ዓለም አቀፍ አጀንዳ እንዲሆን የሚደረገው ጥረት በብዙ መልኩ የሚበረታታ ብሎም የሁሉንም ድጋፍ እና ቀና ትብብር የሚጠይቅ፤ ፈጥኖ መንቀሳቀስንም የሚሻ ነው።

ሠላም ከግለሰብ የሚጀምር ለማኅበረሰብም ሆነ ለሀገር ሕልውና ወሳኝ አቅም ነው። ነገን በብዙ ተስፋ ለሚጠብቀው የሰው ልጅ የሠላም ጉዳይ የማሰብ አቅሙን በአግባቡ ከመጠቀም ጀምሮ፤ የሚያስበውን ተጨባጭ አድርጎ ነገዎቹን ብሩህ ለማድረግ ለሚያደርጋቸው ጥረቶች ስኬት የማይተካ ሚና አለው።

ያለ ሠላም ነገን ቀርቶ ዛሬን በአግባቡ ማሰብ አይቻልም፤ ይህ ዓለም አቀፋዊ እውነታ ነው። በቀደሙት ዘመናት ከሠላም እጦት ጋር በተያያዘ ዓለም የከፈለው ያልተገባ ዋጋ፤ በሰው ልጆች ጥቁር ታሪክነት ተመዝግቦ የሚገኝ ነው። ለሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን ለተፈጥሮ አካባቢ ሠላም የቱን ያህል እንደሚያስፈልግ ሕያው ማስተማሪያም ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ዓለማችን በየዘመኑ የተለያዩ ጦርነቶች እና የርስ በርስ ግጭቶችን አስተናግዳለች። በእነዚህም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ለሞት እና ለአካል ጉዳተኝነት ተዳርገዋል፤ ቁጥር ለመገመት የሚያዳግት ሀብት ወድሟል። አንዳንድ ጦርነቶች እና ግጭቶች ፈጥረውት ያለፉት የሥነልቦና ስብራት ዛሬም ጠባሳው በአግባቡ አላገገመም።

ይህም ሆኖ ግን ዛሬም በዓለማችን አራቱም ማዕዘናት ጦርነቶች እና ግጭቶች አሉ። በነዚህም ከቀደሙት ዘመናት በከፋ መንገድ ሚሊዮኖች ለሞት እና ለአካል ጉዳተኝነት እየተዳረጉ ነው። በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ከሠላማዊ ሕይወታቸው ተፈናቅለው አስቸጋሪ ሕይወት እየገፉ ነው። በትሪሊዮን የሚቆጠር ሀብትም እየወደመ ነው።

ችግሮችን በሠላማዊ መንገድ በድርድር ከመፍታት ይልቅ፤ አሁናዊ አቅምን ታሳቢ ባደረገ መንገድ ልዩነቶችን በኃይል ለመፍታት የሚደረግ ጥረት እየሰፋ ነው። ብሔራዊ ጥቅሞችን ሰጥቶ በመቀበል በፍትሐዊነት ከማስጠበቅ ይልቅ በሴራ ተጨባጭ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ዓለምን ወደ አልተገባ የሠላም እጦት እየወሰዳት ነው።

በአንድ በኩል የተሻለች ዓለም ለመገንባት የሚያስችል አዲስ የዓለም ሥርዓት ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ፤ በዚህም ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሕይወትን በብዙ መልኩ እያቀለለ ባለበት አሁንዊ ዓለም፤ አለመግባባቶችን በሠላማዊ መንገድ በድርድር መፍታት አለመቻል ዓለማችንን ሁለት ገጽታ እንድትላበስ አድርጓታል።

ይህ ተጨባጭ እውነታ ከሁሉም ለአፍሪካ ሀገራት "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" ሆኖባቸዋል፤ እነዚህ ሀገራት እና ሕዝቦቻቸው ለእነዚህ ዓለም አቀፍ እና አካባቢያዊ መልክ ባላቸው ግጭቶች ሰለባ እየሆኑ ነው። ከድህነት እና ኋላቀርነት ለመውጣት ለሚያደርጉት ትግልም ተጨማሪ ፈተና እየሆነባቸው ነው።

በብዙ መልኩ በተሳሰረው አሁናዊው ዓለም የሚፈጠሩ ግጭቶች እና ጦርነቶች መላውን ዓለም በአንድም ይሁን በሌላ መንካታቸው የማይቀር ነው። ለዚህም የሩሲያ ዩክሬን ጦርነትን፤ በመካከለኛው ምሥራቅ፤ በእሥራኤል ሀማስ፣ በእሥራኤል ሂዝቦላ፣ በየመን እና በሱዳን ወዘተ ያሉ ግጭቶችን ማየት በራሱ ተገቢ ነው።

እነዚህ ጦርነቶች እና ግጭቶች አጠቃላይ በሆነው የዓለም የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ አሰላለፍ ላይ እየፈጠሩት ያለው ተፅዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ዓለማችንን ወደ ከፋ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ምስቅልቅል ውስጥ ሊከታት እንደሚችል የብዙዎች ስጋት ነው። ከዚህ ዓለም አቀፋዊ ፈተና ነፃ ሊሆን የሚችል ሀገር ሆነ ሕዝብ ሊኖር አይችልም ።

ከስጋቱ ለመውጣት ያለው አማራጭ፤ ስለ ሠላም ድምፅን ከፍ አድርጎ ማሰማት፤ ችግሮችን ዘመኑን በሚዋጅ የሠላም ድርድር/ውይይት መፍታት፤ ለዚህ የሚሆን ዓለም አቀፍ ትብብር መፍጠር ነው። ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ ትናንት ያስተባበረችው አሕጉር አቀፍ የሠላም ኮንፈረንስ የሚኖረው ሚና እጅግ ትልቅ ነው፡፡ ከትናንት የጦርነት እና የግጭት ታሪኮች በመማር ስለ ሠላም አብዝቶ ማዜም፤ ለስኬታማነቱም ከሁሉም በላይ ዓለም አቀፍ አጋርነት መፍጠር ነው።

በተለይም አፍሪካውያን ከቅኝ ግዛት ነፃነት ማግስት ጀምሮ የሚፈታተናቸውን የሠላም እጦት ለዘለቄታው ለመፍታት የሠላማቸው ባለቤት ሊሆኑ ይገባል። ለሠላማቸው ማንንም ሳይጠብቁ ራሳቸው መፍትሔ መሆንም ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ የሚሆን አጋርነት እና ሁለንተናዊ ቁርጠኝነት ለመፍጠርም ከዛሬ የተሻለ ሌላ ቀን አይኖርም!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሠላም የትምህርት ዘርፍ ልማት እስትንፋስ ነው!

**ወንድይራድ ሰይፈሚካኤል**

የፀጥታ መደፍረስ ቀጥተኛና ከፍተኛ ጉዳት ከሚያደርስባቸው ዘርፎች መካከል አንዱ ትምህርት ነው። የሠላም እጦት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ እና የትምህርት ተቋማት ጉዳት እንዲደርስባቸው በማድረግ በትምህርት ዘርፉ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል። በሠላም እጦት ሳቢያ ትምህርት ቤት ውስጥ መዋል የነበረባቸው ሕፃናት፣ ታዳጊዎችና ወጣቶች ከትምህርት ገበታ ውጭ ሆነው ለተለያዩ አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ጫናዎች ይጋለጣሉ፤ የአላስፈላጊ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች ተገዥ ይሆናሉ።

ሀገር ባቀደችው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት አምራች ዜጎችን ሳታገኝም ትቀራለች። እነዚህ አስከፊ ጫናዎች ሁሉ ተደምረው የሀገሪቱን ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት በእጅጉ ወደኋላ ይጎትቱታል።

የትምህርት ሚኒስቴር የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አፈፃፀም ሰሞኑን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰው ሀብትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲገመገም፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ትምህርት መከታተል ከነበረባቸው 32.5 ሚሊዮን ተማሪዎች መካከል በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙት 24.5 ሚሊዮን እንደሆኑ ተገልጿል። የተቀሩት ግን ከተፈጥሮ አደጋና ከሠላም እጦት ጋር በተያያዘ በትምህርት ገበታቸው ላይ እንዳልተገኙ ተጠቁሟል። ከአኃዞቹ መረዳት የሚቻለው ከስምንት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጭ ሆነዋል። ይህ እጅግ አሳሳቢ ነው።

ይህን ያህል ተማሪ ከትምህርት ገበታ ቀርቶ፣ አንድም ተማሪ ከትምህርት ገበታ ውጭ ሲሆን ሀገር በብዙ መልኮች ለጉዳት ትዳረጋለች። ሀገር ‹‹ተምረው ችግሬን ይፈቱልኛል›› ብላ በተስፋ የምትጠብቃቸው ተማሪ ልጆቿ በሠላም እጦት ምክንያት ከትምህርት ገበታ ውጭ ሲሆኑ፣ ችግሯን መፍታት ይቅርና፣ ተጨማሪ ችግር ይሆኑባታል። የተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጭ መሆን በተማሪዎቹ ብቻ ሳይሆን በወላጆችና በኅብረተሰቡ ላይም አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ያሳድራል። ይህም ቀውሱ ከጥቂት ግለሰቦች ተሻግሮ ማኅበረሰብ አቀፍ ችግርን ያዋልዳል።

ስለሆነም በተለይ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚስተዋሉ ግጭቶች አፋጣኝ መፍትሔ በማበጀት ሠላምን ማስፈንና የትምህርት ዘርፉን መታደግ ይገባል። ሠላምን ማስፈን ሲባል ደግሞ ዘለቄታዊነት ያለው ሠላም ማስፈን መሆን አለበት። በተለይ ደግሞ የኃይል አማራጭ ዘላቂ ሠላምን እውን ማድረግ እንደማይችል ማመን ይገባል፤ ሁሉም ወገን ለሐቀኛና መተማመን ለሰፈነበት የሠላም ድርድር ዝግጁና ቁርጠኛ መሆን ይኖርበታል።

ከተፈጥሮ አደጋ ጋር በተያያዘ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታትም እንዲሁ እንደ ምገባ መርሐ ግብር ያሉትን በስፋት በመተግበር ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱና ተረጋግተው እንዲማሩ ለማድረግ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል። የምገባ መርሐ ግብር በሌሎች ሠላም በሰፈነባቸው አካባቢዎችም የሚተገበር እንደመሆኑ በእነዚህ አካባቢዎችም በልዩ ሁኔታ መተግበር ዜጎችንም የትምህርት ሥርዓቱንም መታደግ ይገባል።

ሠላምን አስፍኖ ከትምህርት ውጭ የሆኑ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ገበታቸው መመለስ እንዲሁም በተፈጥሮ አደጋ ሳቢያ ከትምህርት ገበታ ውጪ ያሉትንም በምገባ መርሐ ግብር ማቀፍ ብቻቸውን ሀገራዊ የትምህርት ዘርፍ እቅድን ለማሳካት በቂ እንዳልሆኑም መገንዘብ ይገባል።

የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ የዘርፉን እቅድ ለማሳካት ከበርካታ ባለድርሻ አካላት ብዙ ጥረቶችን ማድረግ ይጠበቃል። በቅርቡ ወደ ትግበራ የገባውን የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓትና የተሻሻሉ አሠራሮች ትግበራን እስከመገምገም የዘለቀ ተግባር በማከናወን ውጤቱን መተግበር ያስፈልጋል።

በኢትዮጵያ ሥራ ላይ የነበረው የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ለትምህርት ዘርፍ መሻሻልና የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራት አዎንታዊ አስተዋፅዖዎችን እንዳበረከተ ባይካድም፣ ዓይነተ ብዙና ውስብስብ ችግሮችም ነበሩበት። ምክንያቱ ከአቅም ጋር ሊያያዝ ይችላል፤ የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ በንድፈ ሀሳብ እንጂ የተግባር ክህሎትና ፈጠራ ላይ ያተኮረ አይደለም። የምዘና ሥርዓቱም ለተግባራዊ እውቀት ትኩረት የሰጠ አልነበረም።

ሥራ ፈላጊ እንጂ ሥራ ፈጣሪ ትውልድ እየተፈጠረ አይደለም። የምርምርና የቴክኖሎጂ ሥራው ጎልብቶ ኢኮኖሚውን በሚፈልገው መጠን ሲያግዝም አይስተዋልም። ከትምህርትና ሥልጠናው እውቀት፣ ክህሎትና የሥራ ፈጣሪነት አመለካከት በበቂ ሁኔታ ይዞ ከመገኘት ይልቅ ትውልዱ ዲግሪና ዲፕሎማ (ወረቀት) አምላኪ ሆኗል። ይህም የትምህርት ዘርፉን ጉዞ አሳሳቢ እንዲሆን አድርጎት ቆይቷል።

የአንድ ሀገር የትምህርት ሥርዓት መበላሸት የሀገሪቱ ሕልውና አደጋ ውስጥ እንደገባ ሁነኛ ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል። ሠላም የሰፈነባት፣ ማኅበራዊ መረጋጋት ያለባት፣ ምጣኔ ሀብቷ ያደገና ፖለቲካዋ የሰከነ ሀገር እውን ማድረግ የሚቻለው ጥራት ባለው የትምህርት ሥርዓት የተገነባ ትውልድ ማፍራት ሲቻል ነው። ጥራት በሌለውና በወደቀ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ያለፈ ትውልድ ለሀገር ሕልውና ትልቅ አደጋ ይሆናል። ለዚህም ነው ‹‹አንድን ሀገር ለማፍረስ ጦር ማዝመት ሳያስፈልግ፣ የሀገሪቱን የትምህርት ሥርዓት ማበላሸት በቂ ነው›› የሚባለውን ሃሳብ በተደጋጋሚ የምንሰማው።

በራሳቸው የሚተማመኑ፣ በምክንያታዊ ትንተና የሚያምኑ፣ በሙያቸው ብቃት ያላቸው፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣ አዳዲስ ግኝቶችን አፍላቂዎች፣ ጠንካራ የሥነ ምግባርና ግብረገባዊ እሴቶችን የተላበሱ፣ ለሕግ ዘብ የቆሙ፣ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ብቁ ዜጋ ሆነው አጠቃላይ ሰብዕናቸው የተገነባ ዜጎችን ማፍራት የሚቻለው ጥራት ባለው የትምህርት ሥርዓት ነው።

አንዲት ሀገር ሁለንተናዊ እድገትን በማምጣት የሕዝቦቿን ኑሮ ማሳደግ የምትችለው በሚኖራት የሰው ኃይል እምቅ አቅም ነው። የሰው ኃይል መገንቢያው ዋነኛው መሣሪያ ደግሞ ትምህርት ነው። አስተማማኝና ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት ብቸኛው መንገድ ጥራት ያለው የትምህርት ሥርዓትን መዘርጋት ነው። ‹‹ዋናው ሽፋን/ብዛት ነው፤ የጥራቱ ጉዳይ ቀስ ብሎ ይታሰብበታል›› የተባለው አካሄድ ለኢትዮጵያ ምን እንዳቆያት አይተናል። የትምህርት ሥርዓቱ ብልሽት ሀገሪቱን ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል፤ እያስከፈላትም ይገኛል፤ የዚያ ሥርዓት ትምህርት መዘዝ ገና ብዙ ዋጋ ያስከፍላል።

የትምህርት ጥራትን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ተማሪዎችን ያማከለ ዘመናዊና አሳታፊ የመማር ማስተማር ሂደት መከተል፤ የመምህራንን ጥራትና ተነሳሽነት ማጎልበት፤ ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደትን መከተል፤ ተማሪዎችን ማነቃቃት፤ ጠንካራ የትምህርት ቤት አመራርን ማብቃት፤ ምቹና ጤናማ የትምህርት አካባቢ መፍጠር፤ የማስተማሪያ ግብዓቶች ማሟላት እንዲሁም የተማሪዎች ሥነ ምግባርን ማሳደግ ይገባል።

የተማሪዎች ትምህርታቸውን በሚገባ የመከታተል፤ የመምህራን በጥራት የማስተማር፤ የትምህርት አመራር ስትራቴጂካዊ አመራር የመስጠት እንዲሁም የወላጆች ልጆቻቸውን በንቃት የመከታተልና የመደገፍ ተግባራት በቅንጅት ሊከናወኑ ይገባል። በትምህርትና ሥልጠና በቂ የሰው ኃይል ለማፍራት ባለፉት ዓመታት የትምህርትን ተደራሽነት፣ ፍትሐዊነት፣ አግባብነትና ጥራትን ለማጎልበት የተሠሩ ሥራዎች ያስገኙትን ውጤት ገምግሞ ጠንካራውን ማስቀጠል፣ ጎታቹን ማራገፍ ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ በሥነ ምግባር፣ በመልካም እሴትና በብቃት የታነጸ ዜጋን ለማፍራት በሚያስችል መንገድ የተቀረፀ፣ የሀገሪቱን ዕድገትና አንድነት የሚያስቀጥል እንዲሁም ሥራ ጠባቂ ከመሆን ይልቅ ለሥራ ፈጣሪነትና ለሀገር በቀል እውቀቶች ተገቢውን ትኩረት የሰጠ መሆኑን በሚገባ መፈተሽና ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የተሻለ የፈተና ውጤት የሚመዘገበው፣ ጥራት ያለው የትምህርት ሥርዓት ሲኖር ነው!

የትምህርት ሥርዓቱን/የመማር ማስተማር ሥራ በተግባር ተኮር እውቀት በመደገፍ ሥራ ፈጣሪ ትውልድ ለማፍራት መጣር ያስፈልጋል። አዲሱ የትምህርት ሥርዓት ይህን ጥረት እውን ለማድረግ ትልቅ እገዛ ያደርጋል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል። ስለሆነም በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት ሥራ ፈጣሪነትን ባሕሉ ያደረገ ትውልድ እንዲፈጠር የትምህርት ሥርዓቱን ትግበራ በከፍተኛ ጥንቃቄና ትጋት መምራት ይገባል!

በቅድሚያ ግን ለሠላም በተለይ ለዘላቂ ሰላም ጉዳይ ትኩረት መስጠት ይገባል! ሁሉም ነገር በሠላም ማሕቀፍ ውስጥ የሚፈጸም ነውና።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

ነፃ ሃሳብ

# ወቅቱ የቡና ነው!

ኃይሉ ሣህለድንግል

ወቅቱ የቡና ነው፡፡ በርግጥም የቡና ነው፤ በቡና አብቃዩ የገጠሩ አካባቢ ቡና የሚለቀምበት፣ የሚፈለፈልበት፣ ወዘተ ወቅት ነው፡፡ በዚህ ወቅት የአካባቢው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ይሟሟቃል፡፡ የቡና ባለቤቶች ብቻ አይደሉም በዚህ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ባተሌ የሚሆኑት፡፡ የቡና ልማቱ እየሰፋ እንደ መምጣቱ በርካታ ቡና ለቃሚዎች በዚህ ሥራ ይሰማራሉ፡፡ እሸት ቡና ተፈልፍሎ ታጥቦ ለውጭ ገበያ ዝግጁ የሚደረግበት ወቅት እንደ መሆኑ በዚህ ታላቅ ሥራ ሰፊ የሰው ኃይል ይሰማራል፡፡ እናም ቡና የሚለማባቸው አካባቢዎች እንቅስቃሴ በብዙ መልኩ ይሟሟቃል፡፡

በአንዳንድ ቡና የሚለማባቸው ሰፊ አካባቢዎች ለዚህ ሥራ የአካባቢው ማህበረሰብ ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል ፤ ራቅ ካሉ አካባቢዎች ሠራተኞች ለቡና ለቀማ የሚፈለጉበት ሁኔታ እንደነበርም አስታውሳለሁ፡፡ አሁን ለአካባቢው ማህበረሰብ ትልቅ የሥራ እድል የሚፈጠርበት ወቅት እንደመሆኑ የሰው ኃይል ከሩቅ መማተር ላይኖር ይችላል፡፡

ወቅቱን የቡና ወቅት የሚያደርጉት ሌሎች ምክንያቶችም አሉ፡፡ ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው ቡና ሁለት ዓይነት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እነዚህ የቡና ዓይነቶች ኮሜርሻል እና ስፔሻል ቡና ይባላሉ፡፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለውጭ ገበያ ከሚቀርበው ቡና ኮሜርሻሉ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዝ ነበር፡፡ ይህ ቡና ከስፔሻል ቡና አኳያ ሲታይ የሚሰጠው ዋጋ ዝቅተኛ ነው፤ ስፔሻሊቲ ቡና ግን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል፡፡

ኢትዮጵያም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚህ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በሚያስገኘው የቡና ዓይነት ላይ በትኩረት እየሠራች ትገኛለች፡፡ ይህን ተከትሎም ለውጭ ገበያ የሚላከው ስፔሻሊቲ ቡና በመቶኛ እየጨመረ ይገኛል፡፡ ይህ መልካም እድል ደግሞ የቡናውን ጥራት ለመጠበቅ በሚከናወኑ ሰፋፊ ሥራዎች በቡና ላይ የሚሰማራውን ሠራተኛ ቁጥር ይጨምረዋል ተብሎ ይገመታል፡፡

ሀገርንም አምራቹንም ላኪውንም በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችለው ይህ የቡና ዓይነት መሆኑ በእጅጉ ታምኖ ለስፔሻሊቲ ቡና ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ያለበት ሁኔታ ቡና የሚለቀምበትን፣ የሚታጠብበትንና የመሳሰሉት ሥራዎች የሚከናወንበትን ይህን ወቅት ወሳኝ ያደርጉታል፡፡

ቡና አዘጋጆች፣ አቅራቢዎች፣ ላኪዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት በዚህ ወቅት ሥራ ላይ ያውላሉ፡፡ የፋይናንስ ተቋማት በገንዘብ አቅርቦትና ዝውውሩ በንቃት ይሳተፋሉ፤ የመንግሥት አካላትም እንዲሁ ቡናው በወቅቱ ተሰብስቦ በጥራት ተመርቶ ለገበያ እስከሚቀርብ ድረስ ቅድሚያ የሚሰጡት ሥራ አይኖራቸውም፡፡ ለእዚህ ሥራ ድጋፍ በማድረግ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ይጠመዳሉ፡፡

ልማቱ በሚካሄድበት አካባቢ ለተሰማራው ማህበረሰብ እንደ ምግብ፣ የትራንስፖርት አገልግሎትና የመሳሰሉትን የሚያቀርቡ በጣም በርካታ ናቸው፡፡ በቡና ላይ የሚካሄደው ተግባር ከቡና ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸውን የሸቀጣ ሸቀጥና የአልባሳት መደብሮች፣ በአጠቃላይ ግብይቱን ጭምር የተሟሟቀ ያደርገዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ እንቅስቃሴዎች ወቅቱ የቡና ወቅት መሆኑን በሚገባ ያመለክታሉ፡፡

ቡና በሚለማባቸው ክልሎች ከቡና ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ በሚደረግበት በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ ቡና ለውጭ ገበያ በመላክ ከዓለም አቀፍ የቡና ገበያ የምታገኘው የውጭ ምንዛሬ እያደገ መሆኑን የሚያመለክቱ መረጃዎች መውጣታቸው ቀጥሏል፡፡ በየአካባቢዎቹ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሚያስተላልፉት መልእክትም ይህንኑ የሚጠቁም መሆኑ እንዳለ ሆኖ የቡና የውጭ ገበያው መረጃዎች ለአልሚውም፣ በንግዱ ሥራ ለተሰማራውም፣ ለሀገርም ወዘተ ትልቅ የምስራች መሆናቸው መታወቅ ይኖርበታል፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ሀገሪቱ ባለፉት ዓመታት ወደ ውጭ የምትልከው የቡና መጠንም የምታገኘው የውጭ ምንዛሬም በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡፡ ይህን ስኬት ማስመዝገብ የተቻለው በቡናው ዘርፍ የተካሄደውን ሪፎርም ተከትሎ መሆኑ በመንግሥት በኩል በተደጋጋሚ ተጠቁሟል፡፡ ሪፎርሙ ወደ ውጭ የሚላከውን የቡና መጠን እንዲሁም ከቡናው የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ መጠን ማሳደግ አስችሏል፡፡ ወደ ውጪ የሚላከው ቡና እየጨመረ መጥቶ ባለፈው በጀት ዓመት ከ300 መቶ ሺ ቶን በላይ ቡና ለውጭ ገበያ ማቅረብ ተችሏል፤ በዚህም ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊየን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ተገኝቷል፡፡

> **መንግሥት በቡና ላይ ይህን ያህል ተስፋ ሰንቆ እየሠራ ባለበት ወቅት ከቡና ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው አካል በሙሉ ቡና በጥራት ተመርቶ ለዓለም ገበያ በሚቀርብበት ሁኔታ ላይ ሁሉ እንደ ሀገርና ሕዝብ ሆኖ መሥራት ይኖርበታል**

ሌላው በቡናው ዘርፍ የተመዘገበው ስኬት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኝ በሚችለው ስፔሻሊቲ ቡና ላይ የተመዘገበው ነው፡፡ የቡናና ሻይ ባለሥልጣን መረጃ እንዳመለከተው፤ የዛሬ ሶስት ዓመት ለውጭ ገበያ ከሚቀርበው ቡና የኮሜርሻል ቡና መጠን በመቶኛ ሲታይ 70 በመቶውን፣ የስፔሻሊቲ ቡና መጠን ደግሞ 30 በመቶውን ይሸፍኑ ነበር፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ ሁኔታ ተለውጧል፤ የስፔሻሊቲ ቡና በአሁኑ ወቅት ከፍተኛውን እጅ እንዲያዝ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም ለውጭ ገበያ ከሚቀርበው ቡና 60 በመቶው ስፔሻሊቲ ቡና እንዲሆን የተደረገ ሲሆን፣ የኮሜርሻሉን ወደ 40 በመቶ ማውረድ ተችሏል፡፡ በቀጣይም ከዚህ በታች ለማውረድ እንደሚሰራ ይጠበቃል፡፡

በሪፎርሙ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን የቡና መጠን ማሳደግ ተችሏል፡፡ ከሪፎርሙ በፊት ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ቡና 200 ሺ ቶን ደርሶ እንደማያውቅ የቡናና ሻይ ባለሥልጣን መረጃ ያመለክታል፡፡ በ2016 በጀት ዓመት ይህን አሀዝ ወደ 300 ሺ ማሳደግ ተችሏል፡፡

ይህ ሁሉ ለውጥ በከፍተኛ ርብርብ የተገኘ ነው፡፡ ይህን ለውጥ አሁንም ማስቀጠል ወሳኝ ነው፤ መንግሥትም ወደ ውጭ የሚላከውን የቡና መጠንም ሆነ ከዚህ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ለማሳደግ አቅዶ እየሠራ ነው፡፡ መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ በተያዘው 2017 በጀት ዓመት ከቡና የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ሁለት ቢሊየን ብር የሚጠጋ ለማድረስ ታቅዷል፡፡ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ወደ ውጭ ከተላከ ቡና የተገኘው የውጭ ምንዛሬ ጥሩ አፈጻጸም ይህን እቅድ ማሳካት እንደሚቻል ያመላከተ ተብሏል፤ ባለፈው ጥቅምት ወርም ተመሳሳይ ስኬት መመዝገቡን መረጃዎች እየጠቆሙ ሲሆን፣ በዘርፉ የሚደረገውን ርብርብ ይበልጥ በማጠናከር ለእዚህ ስኬት መሥራት አሁንም በእጅ ያስፈልጋል፡፡

ከፍ ብዬ እንዳመለከትኩት ቡና ላይ በትኩረት መሠራቱን ተከትሎ ነው ይህ ሁሉ ለውጥ የመጣው፡፡ አሁንም ከቡና የሚገኘውን ጥቅም ማሳደግ እንደሚቻል ታምኖበት እየተሠራ ነው፡፡ ከቡና ዘርፍ ተጠቃሚ ለመሆን በልማቱ እየተከናወኑ ያሉ ሰፋፊ ሥራዎች እንዳሉ ሆነው በግብይቱ ላይ በትኩረት ለመሥራት የተያዘው እቅድ እንዲሳካ ለማድረግ መላው የቡና ቤተሰብ ተቀናጅቶ መሥራት ባለበት ወቅት ላይ እንደሚገኝ ለማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡ ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት የቡና ቤተሰቦች በጣም በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህ ቤተሰቦች ከገጠር አንስቶ በከተሞች፣ በመላው ዓለም ጭምር የሚሠሩ ናቸው፡፡ በእዚህ ከቡና ብዙ በሚጠበቅበት ዘመን እነዚህ ተዋንያን በሙሉ በማነቃነቅ በጋራ አብረው መሥራታቸውን እንዲያጠናክሩ ማድረግ ይገባል፡፡

በተለይ በአሁኑ ወቅት ቡና በሚለቀምባቸው፣ በሚታጠብባቸውና በአጠቃላይ በሚዘጋጅባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች በሙሉ ለቡና ጥራት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ቡናው ገዥዎች እጅ እስከሚገባ ድረስ በእያንዳንዱ መዳረሻ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግን የሚጠይቅ ሰብል እንደመሆኑ ሲለቀም፣ ሲታጠብ፣ ሲከማች፣ ሲጓጓዝና ሲላክ በሁሉም ምዕራፍ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡

ሀገር ከዚህ ቡና ብዙ ትጠብቃለች፤ አርሶ አደሮችም ላኪዎችና አቅራቢዎችም ከዚህ ቡና ብዙ ይጠብቃሉ፤ የሚጠብቁት እውን መሆን የሚችለው አንድም ቡና በጥራትና በጥራት ብቻ ተዘጋጅቶ ለውጭ ገበያ ሲላክ ነው፡፡ የመጋዘኖች፣ የማጓጓዣዎች፣ የማሸጊያ ጆንያዎች ከኬሚካል ከመሳሰሉት የጸዱ መሆን ወሳኝ ነው፡፡ ከጥራት አኳያ በእዚህ ልክ ከተሠራ ከቡና የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ማስጠበቅ ይቻላል፡፡

የውጭ ምንዛሬ ግኝቱን ለማሳደግ የቡናን ጥራት ከማስጠበቅ ጎን ለጎን ገበያው በፈጠረው መልካም እድል ለመጠቀም አተኩሮ መሥራትም ያስፈልጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ቡና ጥሩ ዋጋ ያለው ስለመሆኑ ሀገሪቱ ባለፉት አራት ወራት ከቡና ያገኘችው ገቢ ያመለክታል፡፡ ገበያው በደራበት በአሁኑ ወቅት ቡናውን በሙሉ ወደ ገበያ ማውጣት ይገባል፡፡

የተሻለ ዋጋ መጠበቅ ክፋት ባይኖረውም የቡና ዋጋ በዓለም አቀፍ ገበያ የሚወሰን መሆኑ ይታወቃል፡፡ ዋጋው አንዳንዴ ሊወርድ የሚችልበት ሁኔታ ሊያጋጥም የሚችል ስለመሆኑ ያለፉ ተሞክሮዎች ያስገንዝባሉ፡፡ የተሻለው አማራጭ ገበያው ጥሩ በሆነበት በአሁኑ ወቅት ቡናውን ለገበያ በማቅረብ ራስንም ሀገርንም መጥቀም ነው፡፡

ቡና እንዳይባክን ማድረግ ላይ መሥራትም ሌላው ተግባር ነው፡፡ ቡናው በወቅቱ ገበያ ካልወጣ ሊባክን የሚችልበት እድል ሰፊ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለውጭ ገበያ ቀርቦ ለዜጎችም ለሀገርም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኝ የሚችልን ቡና በሀገር ውስጥ ባልተገባ መልኩ ጥቅም ላይ ማዋል ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል፤ ሰፋ አርጎ በማሰብ ሀገር በእጅጉ የምትፈልገውን የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ሌላው ሀገሪቱ ከቡና የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ እንዳትሆን ሲያደርጋት የኖረው የኮንትሮባንድ ንግድ ነው፡፡ የሀገሪቱን ቡና ጨምሮ የቁም እንስሳት፣ ወርቅን ጨምሮ የተለያዩ ማዕድናት፣ የተለያዩ ዓይነት እህሎች ወደ ጎረቤት ሀገሮች በሕገ ወጥ መንገድ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

የኢትዮጵያ ቡና ወደ ጎረቤት ሀገሮች በኮንትሮባንድ እንዲወጣ እየተደረገ አንድም እግር ቡና የሌላት አንድ የጎረቤት ሀገር ከቡና ላኪ ሀገሮች ተርታ የተሰለፈችበት ሁኔታ እንደነበርም ሲጠቀስ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ከዚህም ምን ያህል የሀገሪቱ ቡና በኮንትሮባንድ እንደሚወጣ መረዳት ይቻላል፡፡

ሀገሪቱ በቡና ልማትም ግብይትም ብዙ ርቀት ለመጓዝ እቅዱ እንዳላት ይታወቃል፡፡ በቡናው ዘርፍ እንደ ሀገር የሚላከውን ቡና መጠን በመጨመር የሚገኘውንም የውጭ ምንዛሬ ማሳደግ ላይ የሚከናወነው ተግባር አንድ ነገር ሆኖ ከዓለም ቡና አምራች ሀገሮች ልቆ ለመውጣት ታቅዶ እየተሠራም ነው፡፡ በቡና ምርታማነት ኢትዮጵያን ከሚበልጡት ብራዚልና ቬትናም ጋር ለመወዳደር ታስቧል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ፤ ዘንድሮ ከብራዚልና ከቬትናም በስተቀር በቡና ምርታማነት ኢትዮጵያን በዓለም የሚበልጣት ሀገር አይኖርም ሲሉ ጠቅሰው፣ በርካታ ሀገራትን አልፈን መጥተን አሁን የቀሩን ብራዚልና ቬትናም ናቸው ብለዋል፡፡ ለሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት የጀመርነውን የቡና ተክል ጉንደላና ችግኝ ተከላ አጠናክረን ከቀጠልን ከብራዚል በስተቀር በቡና ምርት ኢትዮጵያን የሚበልጣት ሀገር እንዳይኖር ታቅዶ እየተሰራ ነው ሲሉም አስታውቀዋል፡፡

ዘንድሮ ግን ከብራዚልና ከቬትናም ቀጥሎ ሶስተኛዋ ትልቅ ቡና አምራች ኢትዮጵያ መሆኗን ጠቅሰው፣ ከቬትናም ጋር ያለው ልዩነት እንደሚታወቅ፣ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት በሚከናወኑ ሥራዎች ከዚያ ያላነሰ ምርት ማምረት እንደሚቻል፣ ባለፈው ዓመት አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር ከቡና ኤክስፖርት መገኘቱን፣ በዚህ ዓመት ሁለት ቢሊየን ዶላር ገደማ እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል፡፡

የቡና ምርት እያደገ ስለመጣ በሀገር ውስጥ ያለው ተጠቃሚነት ያደገ ቢሆንም ለውጭ ገበያ የምናቀርበውም በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መጥቷል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ዘንድሮ ከአራት መቶ ሀምሳ እስከ አምስት መቶ ሺህ ቶን ድረስ ቡና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ መታቀዱን ተናግረዋል፡፡ የዛሬ አምስት ዓመት አጠቃላይ የኢትዮጵያ ምርት አራት መቶ ሀምሳ ሺህ ቶን አይሞላም ነበር ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ይህ ሁሉ በቡና ላይ በትኩረት የመሥራትን አስላፈጊነት ያስገነዝባል፡፡ ወቅቱ በርግጥም የቡና ነውና ስለቡና ለቡና እንስራ፡፡ በዚህ የቡና ወቅትም ይህን ታሳቢ ያደረገ ሥራ መሥራት ከመላው የቡና ቤተሰቦች ይጠበቃል፡፡ መንግሥት በቡና ላይ ይህን ያህል ተስፋ ሰንቆ እየሠራ ባለበት ወቅት ከቡና ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው አካል በሙሉ ቡና በጥራት ተመርቶ ለዓለም ገበያ በሚቀርብበት ሁኔታ ላይ ሁሉ እንደ ሀገርና ሕዝብ ሆኖ መሥራት ይኖርበታል፡፡

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የቡና ማሽን የሠራው ታዳጊ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ተማሪ ቴዎድሮስ ታደሰ ይባላል። በአዲስ አበባ ከተማ ልደታ ክፍለ ከተማ የእድገት በሥራ ትምህርት ቤት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነው። ቡና በቀላሉ በአጭር ጊዜ ማፍላት የሚያስችል የፈጠራ ሥራ ሰርቷል። የፈጠራ ሥራውም «አጠቃላይ የቡና ማሽን (ኮፊ ፕሮሰሲንግ ማሽን)» ይሰኛል። ይህን የፈጠራ ሥራ ትምህርት ሚኒስቴር በቅርቡ ከባለድርሻ አካላት ጋር ባዘጋጀው ዘጠነኛው ዙር ሀገር አቀፍ የሳይንስና ምህንድስና ቀን አውደ ርዕይ ላይ አቅርቧል።

ተማሪ ቴዎድሮስ ገና በልጅነት እድሜው ይህን የፈጠራ ሥራ ለመሥራት ካነሳሱት ምክንያቶች ዋንኛው በየቀኑ ቡና ሲፈላ የሚመለከተው አሰልቺ(ረጅም) ሂደት ነው። ቡና አጥቦ፣ ቆልቶ፣ ፈጭቶ እስከ ማፍላት ድረስ ባሉት ሂደቶችን ማሳጠርና ጊዜ መቆጠብ የሚቻልበትን ሁኔታ አሰላስሏል። በተለይ ኮንዶሚንየም ቤት መብራት ሲጠፋ ከፎቅ ወደ መሬት ወርደው ቡና ለመውቀጥ ብዙዎች ሲሰላቹም ተመልክቷል። በእነዚህ ምክንያቶች የተነሳ ብዙዎች ቡና ማፍላት ሥራ ሆኖባቸው መጠጣት እየፈለጉ ሲተውትም አስተውሏል።

ተማሪ ቴዎድሮስ ይህን ሁሉ አስተውሎ በቸልታ ማለፍ አልፈለገም፤ ይልቁንም ለችግሩ መፍትሔ ያለውን ሲያሰብና ሲያሰላስል ይቆያል። ቆይታው ከንቱ አልሆነም፤ ቡናን እየተዝናኑ በቀላሉ ማፍላት ቢቻል ሰዎች ቡና እያማራቸው አይቀርም በሚል ቡና በቀላሉ ማፍላት የሚችል የቡና ማሽን መሥራት ችሏል።

የቡና ማሽኑ ቡናውን አፍልቶ እስኪጨርስ ቆሞ መጠበቅ አያስፈልግም። ተቆልቶ ለመጠጣት እስከሚደርስ ድረስ ያሉትን ሂደቶች በቅደም ተከተል ካከናወነ በኋላ መጨረሱን በስልክ ደውሎ ማሳወቅ የሚችልም ነው። ተማሪ ቴዎድሮስ አንድ ሊትር ቡና እንዲያፈላ ታሰቦ የተሠራ መሆኑን ገልጾ «ቡና አጥቦ እስከ ማፍላት ድረስ ያለውን ሂደት በሙሉ በ15 ደቂቃ ውስጥ አከናውኖ ይጨርሳል» ይላል።

ተማሪ ቴዎድሮስ እንዳብራረው፤ ማሽኑ በሀገር ውስጥ አገልግሎት እየሰጡ ካሉት ሌሎች የቡና ማሽኖች ለየት ከሚያደረጉት ምክንያቶች መካከል ዋንኛው በጠባብ ቦታ ላይ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለውን የቡና አፈላል ሂደት አንድ ላይ አጠቃሎ መጨረሱ ነው። በቀላሉ ከቦታ ቦታ ማንቀሳቀስ የሚቻል መሆኑ ሌላኛው ጉዳይ ነው። በተጨማሪም ማሽኑ ቡና እንዲያፈላ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ሳይፈጽም ቢቀር እንኳ በሞባይል ስልክ ላይ ደውሎ በማሳወቅ ማስታወስ መቻሉ ከሌሎች የፈጠራ ሥራዎች ለየት እንዲል ያደርገዋል።

ማሽኑ ቡናውን ለማፍላት ቡና በቤት ውስጥ ሲፈላ የሚከተለውን ሂደት መሠረት ያደረገ ቅደም ተከተል አለው። ማሽኑ አንድ ሊትር ቡና ለማፍላት ታሰቦ የተሠራ ሲሆን በቅደም ተከተሉ መሠረት በቅድሚያ አንድ ሊትር ቡና ለማፍላት የሚያስፈልገው 250 ግራም ቡና ወደ ማሽኑ እንዲገባ ይደረጋል። ይህ አካሄድ ቡናው እንዳይወፍር ወይም እንዳይቀጥን ያደርገዋል። ከዚህ በበለጠ ወይም ባነሰ መጠን የምንጠቀም ከሆነ ግን ቡናው ሊወፍር አልያም ሊቀጥን ይችላል።

የመጀመሪያ ሂደት ላይ ቡናው ወደ ማሽኑ ከገባ በኋላ ማሽኑ ቡናውን አጥቦ እጣቢውን ወደ ተዘጋጀለት ቦታ በማስገባት ያስወግዳል። በመቀጠልም ቡናውን ወደ የሚቆላበት ቦታ እንዲሄድ ይደረጋል። ቡናው በሚገባ ከተቆላ በኋላ ወደ መፍጫው ከመግባቱ በፊት እንዲቀዘቅዝ ያደርጋል፤ ከዚያም ወደሚፈጭበት ቦታ ይገባል። ከተፈጨ በኋላም ወደሚፈላበት ቦታ ገብቶ እንዲፈላ ያደርጋል። ከዚያም ቡናውን በአንድ በኩል፤ አተላውን በሌላ በኩል እንዲወጣ ያደርጋል ሲል ተማሪ ቴዎድሮስ ያብራራል።

ማሽኑ ቡናውን አፍልቶ እስኪጨርስ መጠበቅ የሚፈልግ ሰው አጠገቡ ሆኖ መጠበቅ ይችላል፤ ለመጠበቅ የማይችልና ቡናውን እስኪፈላ ድረስ ሌሎች ሥራዎች መሥራት የሚፈልግ ደግሞ ወደ ሥራው መሄድ እንደሚችልም ያስረዳል። ማሽኑ ልክ ቡናውን ስለመፍላቱ እንዲያሳውቅ በተሰጠው ስልክ መሠረት ደውሎ እንደሚጠቁም አመልክቷል።

ማሽኑ ቡናውን አፍልቶ ሲጨርስና ቡና ጠጪው ወደ ማሽኑ ሲጠጋ ማሽኑ የስኒ ማስቀመጫውን ከማሽኑ ወጥቶ ስኒ በማስቀመጥ ለመቅዳት ዝግጁ እንደሆን ይገልጻል። ማሽኑ ቡናውን አፍልቶ ከጨረሰ በኋላ የሰጠነውን ትዕዛዝ ረስተን ሄደን ከሆነም ስልካችን ላይ ደውሎ ያስታወስናል። ከአካባቢው ርቀን ሄደንም ከሆነ በአካባቢው ያለው ሰው ቡናውን ሳይቀዘቅዝ እንዲጠቀምበት የሚያስችል ሁኔታ እንዳለውም ይናገራል።

እንደ እርሱ ማብራሪያ፤ ማሽኑን ተንቀሳቃሽና ተሽከርካሪ በመሆኑ ማንኛውም ሰው ሊጠቀመው የሚችልና ጊዜ የሚቆጥብ ነው፤ በተለይ በየቤታችን እንደተለመደው ዓይነት የቡና አፈላል ሂደቱን ተከትሎ እንዲፈላ የሚፈልጉ፣ ነገር ግን የማይችሉ ሰዎች ካሉ ማሽኑን ተጠቅመው ቡና መጠጣት ይችላሉ።

ብዙ ሰዎች ጊዜ ስለሌላቸው ቡና መጠጣት እያማራቸው ሳይጠጡ የሚወሉባቸው አጋጣሚዎች እየተፈጠሩ መሆናቸውን ይናገራል። በተለይ አቅመ ደካሞች ቡና ፊታቸው ታጥቦና ተቆልቶ መጠጣት ቢፈልጉም፣ ይህንን ለማድረግ አቅም ስለሌላቸው ሲቸገሩ ይታያል ሲል ጠቅሶ፣ ይህ ማሽን ግን ይህን ሁሉ ችግር እንደሚቀርፍ ያመለክታል።

ማሽኑ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰራ ሲሆን፤ ከወዳደቁና በቀላሉ አካባቢው ላይ ከሚገኙ ቁሳቁስ የተሰራ ነው። ለአብነት ማንቆርቆሪያ እንደ ቡና መቁያ፣ ሽንኩርት መፍጫን እንደ ቡና ማጠቢያ አድርጎ ተጠቅሞበታል፣ የቡና ማሽን ዲናሞን በመቀየር፣ የቡና ማቀዝቀዣ ማሽን እና የኤሌክትሪክ ማብሪያና ማጥፊያዎች መጠቀሙን ይናገራል።

ማሽኑ በአንድ ጊዜ የሚያፈላው አንድ ሊትር ቡና 15 ስኒ ያህል ቡና ሊወጣው እንደሚችል አስታውቆ፣ «ይህ ማለት ደግሞ አስራ አምስት ሰዎችን በአንድ ጊዜ ቡና ማጠጣት ይችላል ማለት ነው» ሲልም ያብራራል። በ15 ደቂቃ ውስጥ አስራ አምስት ሰዎች ቡና ማጠጣት እንደሚችል ተናግሮ፣ ማሽኑ በተለይ ቡና በማፍላት ሥራ ለተሰማሩ ሰዎች በጣም አዋጭ እንደሆነ ይጠቁማል። ለሆቴሎች፣ ለካፌዎችና ለመሳሰሉትም ቡናን በቀላሉና ፈጣን በሆነ ዘዴ ለማፍላት ያስችላል ሲል ያብራራል።

ይህንን የቡና ማሽን ለመሥራት ሲነሳ በሀገር ውስጥ የተሠሩ የተለያዩ የቡና ማሽኖች መመልከቱን የሚናገረው ተማሪ ቴዎድሮስ፤ ከተመለከታቸው ማሽኖች አብዛኛዎቹ የተቆላ ቡና ጨምቀው የሚያፈሉ መሆናቸውን ይገልፃል። አዲሱ ማሽን ግን በቤታችን ውስጥ እንደሚፈላው ቡና ዓይነት ሂደት ባሕላዊ ይዘቱን ጠብቆ እንደሚያፈላም ይገልጻል።

ተማሪ ቴዎድሮስ እነዚህን የቡና ማሽኖች ካየ በኋላ የተለያዩ ሂደቶችን በአንድ ላይ አጠቃሎ ቡና ማፍላት የሚያስችል ማሽን መፍጠር እችላለሁ ብሎ መነሳቱንም ይገልጻል። ቡና ቤት ውስጥ የሚፈላበትን ባሕላዊ የአፈላል ሂደት የተከተለ የአፈላል ሥርዓት ተከትሎ የሚያፈላ የቡና ማሽን መሥራት እንደሚችል አምኖ ተግባራዊ ሊያደርግ እንደቻለም ያመለክታል። ማሽኑ ቡና የማፍላት ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የሚያፈላ ስለመሆኑም በመኖሪያ ቤትም በትምህርት ቤትም ተፈትሾ መረጋገጡን ይናገራል።

«ለዚህ ማሽን ብዙ አውጥቼበታለሁ ብዬ አላስብም፤ ያወጣኋቸው ነገሮች በጣም ጥቂት ናቸው፤ ለማድመቂያ ቀለሞች፣ ለኤሌክትሪክ ገመዶች ፣ ለቻርጅ ቦርዶች እና ለብሬከሮች ብቻ ጥቂት ወጪ አውጥቼለሁ እንጂ ሌሎቹ ከቤት ውስጥ ያገኘኋቸው እቃዎች ናቸው» የሚለው ተማሪ ቴዎድሮስ፤ ማሽኑ እንደሚሰራበት ቁስና እንደሚፈለገው መጠን ዋጋውን መተመን እንደሚቻልም አስታውቋል። ብዙ ወጪ የማያስወጣ መሆኑ በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ማቅረብ እንደሚቻል ያስረዳል።

እንደ ተማሪ ቴዎድሮስ ማብራሪያ፤ አሁን ባለበት ሁኔታ ላይ ሆኖ ዋጋ ለማውጣት ይከብዳል። ምክንያቱም ከዚህ በተሻለ መልኩ መሥራት ይቻላል። ይህ ማሽን ለ15 ሰዎችን ቡና እንዲያጠጣ ታስቦ የተሠራ ነው። ከዚህ በላይ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚፈለግ ከሆነ በዚያ ልክ ለመሥራት የሚያስፈልጉ ቁሳቁስን ከግምት ውስጥ በማስገባት ዋጋ ማውጣት ይቻላል።

ይህን በማሽን ላይ የሚጨመርበት ካለ ጨምሮ፣ የሚቀነሰውም ካለ ቀንሶ በተሻለ መልኩ ለመሥራት ሃሳብ አለው። ማሽኑ በሀገር ውስጥ በስፋት ተመርቶ ሁሉም ሰው ሊጠቀምበት እንዲችል ለማድረግ




የበኩሉን ጥረት እንደሚያደርግም ይናገራል። በተለይ በቡና መፍላት ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚሰሩ ሰዎች ድካማቸውን በማቅለልና ጊዜያቸውን በመቆጠብ በቀላሉ ቡና ማፍላት የሚችሉበት መሆኑን ጠቅሶ፤ ይህ የፈጠራ ሥራ በሚሰራበት ወቅት አንዳንድ ቁሳቁስን ለማሟላት ብዙ ጥረት ማድረጉን አስታውሶ፣ ትምህርት ቤቱ አንዳንድ ወጪዎችን በመሸፈን ድጋፍ እንዳደረገለትም ነው ያመለከተው።

የፈጠራ ሥራን ከልጅነቱ አንስቶ እንደጀመረው አስታውሶ፤ በርካታ የፈጠራ ሥራዎች መሥራቱንም ይናገራል። የፈጠራ ሥራዎቹን ለውድድር አቅርቦ ማበረታቻዎች እንዳገኘባቸውም ይገልጻል። ይህም በፈጠራው እንዲገፋ ብርታትና ጉልበት እንደሆነው ያስረዳል። የቡና ማሽን ሥራው ግን ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገር ደረጃ የቀረበ መሆኑ ይጠቁማል።

በፈጠራ ሥራ የመቀጠል አላማ ያነገበው ተማሪ ቴዎድሮስ፤ የወደፊት እቅዱም ችግር ፈቺ የሆኑ የፈጠራ ሥራዎች በመሥራት የህብረተሰቡን ችግር መቅረፍ መቻል መሆኑን ይገልጻል። ይህንን ማሽን ለሁሉም ተደራሽ ከማድረግ ባሻገር ብዙ እቅድ እንዳለው አመልክቶ፣ «ይህ ማሽን ትልቁ ሥራዬ ነው። እድሉን ካገኘሁ ገና ብዙ በውስጤ ያሰበኳቸውና ብሰራቸው ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የፈጠራ ሥራዎች አሉኝ። እነዚህን ወደ ተግባር ለመለወጥ ጥረት አደርጋለሁ» ይላል።

«ማሽኑን በትምህርት ቤት ያዩ ሁሉ በእጅጉ አድንቀውታል፤ ተገርመውበታልም፤ ይህም ይበልጥ እንድበረታታ ትልቅ ሞራል ሆኖኛል» የሚለው ተማሪ ቴዎድሮስ፣ በቀጣይም ለአሰባቸው ሥራዎች መሠረት ተጨማሪ አቅም እንደሚሆነው ይገልጻል። የፈጠራ ሥራን አሃዱ ብሎ ሲጀምር አካባቢ ተስፋ ያስቆረጡትና ወደኋላ እንዲመለስ ያደረጉት ችግሮች አጋጥመውት እንደነበር አስታውሶ፣ የጀመራቸውን ሥራዎች ባሰበው መልኩ ማስኬድ ሲያዳግተው ተስፋ እየቆረጠ መልሶ እየሞከረ እንደሚቀጥል ይናገራል።

እንደ እርሱ ወደ ፈጠራው ዓለም ለመግባት የሚፈልጉ እምቅ ችሎታ ያላቸው በርካታ ልጆች ሊኖሩ እንደሚችሉ ጠቅሶ፣ እውቀታቸውን ማውጣት እንዳለባቸውም ያስገነዝባል። ይህንን እንዲያደርጉ የሚደግፋቸው ባይኖር እንኳ ሠርተው ማሳየት እንዳለባቸው ያመለክታል። ወደኋላ ሳይመለሱ ደጋግመው በመሞከር የተሻለ እንደሚሰሩ ጠቁሞ፤ ይህ ሲሆን በራሱ ተነሳሽነት እየፈጠረ ይመጣል ብሏል። ሥራቸው ዛሬ ላይ ተቀባይነት የሌለው ቢመስላቸው ተስፋ ቆርጠው ወደ ኋላ ሳይመለሱ እንዲሰሩ አመልክቶ፣ «ሥራቸው የሚፈለግበት የራሱ ጊዜና ወቅት እንዳለው በማሰብ በትጋት መሥራት ይጠበቅባቸዋል» ሲልም ይመክራል።

## ልዩ የምርመራ ዘገባ

# የሪል ስቴቱ ውስጣ ውስጥ ሲፈተሽ!



**(በመልካም አስተዳደርና የምርመራ ዘገባ ቡድን)**

### የመጨረሻው ክፍል

### የሪል ስቴት ልማቱ ፈተና እና ዕድሉች- በኢትዮጵያ

ሪል ስቴት አፓርትመንት፣ የጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ የኢንዱስትሪ፣ የግብርና እርሻ ልማትን የሚጨምር ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው። መንግሥት በየቦታው የሠራቸው ያለማቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮችም ሪል ስቴቶች ናቸው። በአጠቃላይ መሬትና መሬት ላይ የሚሠራ ቋሚ ንብረት የሚያርፍበት ሁሉ ሪል ስቴት እንደሚባል የተለያዩ ድርሳናት ያስረዳሉ።

ኢንጂነር ደሳለኝ ከበደ በ2013 ዓ.ም "ሪል ስቴት ኢንቨስትመንት አስተዳደር እና ግብይት" በሚል መጽሐፋቸው እንደገለጹት፣ ዘርፉ እየተመራ ያለው ለተለያዩ ዘርፎች በተዘጋጁ የተለያዩ ሕጎች ነው። ለአብነት ብንጠቅስ ግንባታው በሚገነባበት ጊዜ በግንባታ ሕጎች፣ ሲሸጥ ንብረት መሸጥ በሚለው ነው። ግብይቱን የሚመራ ከሚዋዋሉት ውል ውጪ ይሄ ነው የሚባል ሕግ የለም። ይህም ሕገወጥ ግንባታ ወይም ደረጃውን ያልጠበቀ ግንባታ እንዲበራከት ያደርጋል።

በሪል ስቴት ግንባታ መንገድ፣ ውሃ፣ የመብራት፣ ስልክ የዘመናዊ የከተማ መገለጫ ስለሆኑ በሥርዓት መዘርጋት አለባቸው። ለልጆች ትምህርት ቤት፣ የጤና አቅርቦት የንግድ ቦታዎች በአግባቡ መሠራት አለባቸው፣ አረንጓዴ ቦታዎችም መኖር አለባቸው። ከዚህ በተቃራኒ በሕገ ወጥነት የሚሠሩ ቤቶች ደግሞ ይህንን አያሟሉም። ሕገወጥ እና በፕላን ያልተደገፉ ግንባታዎች የጊዜ ጉዳይ ነው ይፈርሳሉ። ይህ የሀገሪቱን ጥሪትና ሀብት ማባከን ይሆናል።

ኢንጂነሩ እንደሚያስረዱት፣ ሪል ስቴትን በተገቢው መንገድ ውጤታማ ባደረጉ እንደ ሕንድና ሲንጋፖር ያሉ ያደጉ ሀገራት በዘርፉ ውጤታማ የሆኑት በዘርፉ የሠለጠኑና ትክክለኛ መረጃ ለሕዝቡ ማድረስ የሚያስችል አሠራር በመፍጠራቸው እና በአግባቡ በመተግበራቸው ነው።

የኢትዮ-አሊያስ የጥብቅና ማኅበር መሥራችና የከርከሮች ኃላፊ ጠበቃ አዲስ ሳዲቅ እንደሚያስረዱት፣ መንግሥት የሚገነባቸውን የጋራ የኮንዶሚኒየም ቤቶችን የሚያስተዳድረው የቤቶች ልማት አስተዳደር የሚባል ተቋም በአዋጅ አቋቁሞ ነው። ይሁን እንጂ የገነባቸውን ቤቶች ከማስተዳደር በዘለለ በግል ዘርፉ አማካኝነት የሚለማውን የሪል እስቴት ዘርፍ ማስተዳደር ጥቂቶች ቤት ገንብተው ለአክሲዮን ገዥዎች ከማስተላለፍ ይልቅ እንደፈለጉት ማጭበርበር እንዲችሉ አድርጓል። ሕሊናቸውን አክብረው በታማኝነት ቤት ገንብተው የሚያስረክቡ አልሚዎች ቢኖሩም በርካቶች ግን በተቃራኒው በአቋራጭ ለመክበር ሲጠቀሙበት ቆይተዋል።

በኢትዮጵያ አጠቃላይ የነፃ ገበያ ሥርዓቱ በተለይም ከግንባታ ጋር ተያይዞ በጣም በእንጭጭ ደረጃ ላይ ያለ ነው። ሁሉም እንደሚገነዘበው ኢትዮጵያ ውስጥ ገበያ በትክክለኛ ትርጉሙ ሲሠራበት አይታይም። ፍላጎት መሠረት ተደርጎ ምርት የሚመረትበት፣ በአቅርቦት እና በፍላጎት መካከል ዋጋ የሚወሰንበት ሁኔታ የለም።

አንድ ጊዜ ዋጋ ከጨመረ በኋላ የቱንም ያህል ምርት ቢመረት እና ገበያው ቢጥለቀለቅ ዋጋ የሚቀንስበት ሁኔታ አይታይም። በሌላው ዓለም ዋጋ የሚጨምረው አቅርቦት ሲቀንስ ነው። አቅርቦት ሲጨምር ደግሞ ዋጋ ይቀንሳል፣ ይህ ጤነኛ የሆነ የገበያ ሥርዓት የሚባለው ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ያለው የሪል ስቴት ገበያም በዚሁ መርሕ መመራት አለበት። ኢትዮጵያ ውስጥ የሪል ስቴት ገበያው መሠረታዊ የሚባሉ ፈተናዎች ያሉበት ሲሆን ዋነኛው ፈተና ከመሬት ጋር የተገናኘ ስለመሆኑ ጠበቃው ያስረዳሉ።

በኢትዮ-አሊያንስ አድቮኬሲ ማኅበር ጠበቃ የሆኑት አቶ ቃለእግዚአብሔር ጎሣዬ በበኩላቸው፣ የሪልስቴት ዘርፉ ካሉበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች እንዲላቀቅ የሕግ ማሕቀፍ መኖሩ ወሳኝ ነው። ባለፉት ዓመታት በመንግሥት ደረጃ ሕግ እንዲበጅለት ዓላማ ተደርጎ ሲሠራ ነበር። ይህም ዘርፉን ለመምራት የሚያስችል ረቂቅ ሕግ ነው። ሕጉ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለ በተገቢ መንገድ ዓላማውን ማሳካት የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል ይላሉ።

የቀድሞ የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስትር የነበሩት መኩሪያ ኃይሌ (ዶ/ር) እ.አ.አ 2022 "Urban Land Policy, Housing, and Real Estate Markets in Urban Ethiopia" በሚል ጥናት አድርገዋል። በጥናታቸው በሕገ መንግሥቱ የሕዝብና የመንግሥት ሀብት ተብሎ የተደነገገው መሬት በተገቢው ሁኔታ ተመዝግቦና ባለቤቱ ታውቆ የሚሠራበት ሁኔታ አልተፈጠረም ይላሉ። የሪል ስቴት ዘርፉ ሌላው መሠረታዊ ችግር የካፒታል ፍሰት ነው።

በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለመኖሩ ምክንያት የካፒታል ፍሰት እጥረት አለ። በዚህም ምክንያት ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ወደ ሪል ስቴት ልማት የሚገቡ አካላትም መልካም ሥነ ምግባር ኖሯቸው፣ ተገልጋዩን አክብረው፣ ለተገልጋዩ ታማኝ ሆነው በገቡት ኮንትራት መሠረት ገንብተው እየሠሩ አይደለም ለማለት የሚያስደፍር መሆኑን ይገልጻሉ።

በተጨማሪም የሚስተዋለው ችግር ደግሞ በዘርፉ ያሉ አመራሮች እና ባለሙያዎች የክህሎት ማነስ ነው። በእነዚህ እና መሰል ችግሮች ኢንዱስትሪው ፈተና ውስጥ እንዲወድቅ ሆኗል። ስለሆነም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሪል ስቴት ብዙ መልካም ዕድሎች ቢኖሩትም በአብዛኛው ግን በእነዚህ ችግሮች ምክንያት በአግባቡ ሥራ ላይ የዋለ ነው ብሎ ለማስቀመጥ የሚያስቸግር መሆኑን መኩሪያ (ዶ/ር) ይገልጻሉ።

በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (3) እንደተደነገገው "የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥት እና የሕዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው።" ሲል ይደነግጋል።

የኢትዮጵያ ፀረ ሙስና ኮሚሽን የዋና ኮሚሽነር የጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ሻሜቦ እንደሚሉት፣ ከመሬት ጋር በተያያዘ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ ከሙስና ጋር የተያያዙ ጥናቶች በተቋሙ ተጠንተዋል። ከእነዚህም በ1994 ዓ.ም የተጠናው ጥናት እንዳመላከተው በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ማኅበራዊ የሕዝብ ችግሮች ውስጥ ሙስና በአራተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠ ነበር።

ኮሚሽኑ በ2013 ዓ.ም ባስጠናው ጥናት ደግሞ ችግሩ ተባብሶ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ማኅበራዊ የሕዝብ ችግሮች ውስጥ ሙስና ወደ ሦስተኛ ደረጃ ከፍ ብሏል። በዚህ ውስጥ መሬት እና ከመሬት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሪል ስቴትን ጨምሮ የሚፈጸሙ ሙስናዎች ይገኙበታል።

ከመሬት ጋር ተያይዞ የሚፈጸሙ ያለአግባብ የመበልፀግ ሂደቶች ውስጥ ተሳታፊ የሆኑና በሕገ ወጥ መንገድ ሀብት ለማፍራት የሚንቀሳቀሱ እና ዘርፉን ከሚመሩ የመንግሥት ኃላፊዎች ጋር በመመሳጠር በሙስና ቁልፍ ቦታዎችን የሚወስዱ እና ግንባታ የሚያከናውኑ ግለሰቦች ቁጥራቸው እየተበራከተ መምጣቱን ይገልጻሉ።

አሁን ባለንበት ዘመን በሌሎች ሀገራት የኮንስትራክሽን ዘርፉ በቴክኖሎጂ የታገዘ ነው። ለቤት መሥሪያ የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች ምርጫ እና የግንባታ ሂደቱ በሙሉ ዘመናዊ በሆነ ቴክኖሎጂ ይታገዛል። በኢትዮጵያ የሚካሄደው የግንባታ ሂደቱም ይሁን የቁሳቁስ አጠቃቀሙ ዘመን ያለፈበት እና ኋላቀር ነው።

በዚህ ምክንያት በፍሳሽ አወጋገድ፣ በውሃ አቅርቦት በቴክኖሎጂ (አይሲቲ) አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ከፍተኛ ችግሮች አሉ። በኢትዮጵያ በሚገኙ በአብዛኛዎቹ ሕንፃዎች ላይ የሳተላይት ዲሽ በብዛት ተንጠልጥሎ ይታያል። ይህም የሆነው የቴክኖሎጂ አጠቃቀማችን በጣም ኋላ ቀር በመሆኑ ነው።

በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በሀውሲንግ እና ሪል ፕሮፐርቲ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት አቶ ልሳነወርቅ ስለሺ፣ ኢትዮጵያ ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት ሀገር መሆኗን አስታውሰው፣ ከተሞቿ በጣም በፍጥነት እያደጉ ነው። በውጭ ሀገራት ቀላል ያልሆነ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ዲያስፖራ የሚኖር በመሆኑ አልሚዎች ዲያስፖራውን የሚያታልሉበት ሁኔታ ሰፊ ነው።

በዚህም የተነሳ የሪል ስቴት ዘርፉ ከመቶ ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በሚኖርባት ኢትዮጵያ ለሚቀጥሉት አርባ እና ሃምሳ ዓመታት አጓጊ እና በጣም ትልቅ ገበያ እንደሚኖረው ለማወቅ ሳይንሳዊ ትንተና ወይም የጠለቀ ዕውቀት የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም።

በዘርፉ ያለው መልካም ዕድል ከተሞች እንደገና መሠራት ያለባቸው መሆኑ ነው። አዲስ አበባን ጨምሮ እንደገና መገንባት ያለባቸው ከተሞች አሉ። ከቀደመው ችግር በመነሳት ከተሞቹ በአብዛኛው እንደገና መሠራት ያለባቸው ናቸው።

በአጠቃላይ ከተሞቻችን ዘጠና በመቶ እንደገና መሠራት ያለባቸው ናቸው። በበለፀጉ ሀገሮች ከተሜነት (አርባናይዜሽን) ከ85 እስከ 90 በመቶ ይደርሳል። ከዚያ አኳያ በእኛ ሀገር ከተሜነት ገና ምንም ያልተጀመረ ዘርፍ ነው ማለት ይቻላል። በመሆኑም የሪል ስቴት ዘርፉ ከተሜነትን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ዕድል ይኖረዋል። ስለሆነም ለዜጎች በተመጣጣኝ ዋጋ ቤት የሚያቀርቡ ሪል ስቴቶች ሊኖሩ ይገባል። ይህ ደግሞ ለአልሚዎች መልካም ዕድል የሚፈጥር ነው።

የቤት አቅርቦት እና ፍላጎት ያለመጣጣም ችግር ከየት የመጣ ነው? እንዴትስ ማስተካከል ይቻላል? ለሚለው ጥያቄ አቶ ልሳነወርቅ ስለሺ የቤት አቅርቦት እና ፍላጎቱ አለመጣጣሙ ምክንያት ቀደም ብሎ እንደተጠቀሱት የመሬት አቅርቦት፣ የካፒታል፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና በዘርፉ ላይ ብቁ የሆነ አመራር እና ሠራተኛ ያለመኖር ነው።

ይህ ችግር እንደ ችግር ከቀጠለ ሁለት ትልልቅ ተግዳሮቶችን ያመጣል። ስለሆነም ዜጎች በራስ መተማመን፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ላይ የንብረት ባለቤት ሆነው፣ መምረጥ፣ መመረጥ መቃወም፣ መደገፍ ላይ አቅም ያንሳቸዋል። ምክንያቱም ቤት ያለው ሰው እና ቤት የሌለው ሰው በሞራሉም፣ በራስ መተማመንም፣ ውሳኔ ሰጭነቱ ላይ ተፅዕኖ ስላለው ነው።

አንድ ዜጋ የሀገሩ ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥበት አንዱ መንገድ የቤት ባለቤት ሲሆን ነው። ሰው ተኮር መንግሥትም ይህንን በማድረግ ለዜጋው ክብር የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

ዘርፉ በአግባቡ እና ትኩረት ተሰጥቶት ካልተመራ የቤት አቅርቦቱ በመኪና ፍጥነት ሲሄድ ሕገወጥ ግንባታው ደግሞ በአውሮፕላን ፍጥነት መጓዙ አይቀርም። ስለዚህ ሁልጊዜም የሕግ ማስከበር ሥራ እና የቤት አቅርቦት ላይ የሚደረገው ጥረት ሕገወጥነቱን እንዲከላከል በሚያስችል መልኩ መደረግ አለበት ሲሉ መምህሩ ይመክራሉ።

### ሪል ስቴት እና የዳኞች ፈተና

በሀገራችን ሪል ስቴት አልሚዎች እንጂ ዘርፉ የሚመራበት ሕግ ባለመኖሩ ችግር በተፈጠረ ጊዜ ጉዳዩን በፍርድ ቤት አይቶ ለተበዳይ ፍትሕ ለመስጠት ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውል እና ኮንስትራክሽን ዳኝነት ከፍተኛ ልምድ ካላቸው ሦስት ዳኞች የተገኘን መረጃ እንዲሁም ከፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተገኙ የሰነድ ማስረጃዎችን ዋቢ በማድረግ የሚከተለውን ዘገባ ይዘናል።

### ዳኛ አንድ

ዳኛ በኃይሉ ተዋበ ይባላሉ። በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከውል ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ችግሮችን ይዳኛሉ። ከሪል ስቴት ጋር በተያያዘ የሰጡንን ሙያዊ ማብራሪያ እንደሚከተለው አቅርበናል።

### በሪል ስቴት አልሚዎች እና በገዢዎች መካከል ቤቱ ሳይጠናቀቅ የሚደረግ ውልን በፍርድ ቤት እንዴት ይዳኛል?

የሪል ስቴት ጉዳይ ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተያያዘ ነው። የቤት ሽያጭን በተመለከተ መሠረታዊ ሕጉ ተመሳሳይ ነው። ለሪል ስቴት ተብሎ ራሱን ችሎ የተለየ በሕጉ የተቀመጠ መስፈርት የለም። ስለዚህ ማንኛውም የማይንቀሳቀስ ንብረት በሚሸጥበት የሕግ አግባብ በሪል ስቴት ደረጃ የሚሸጡ ቤቶችም እንዲሸጡ ይጠበቃል።

ያ ማለት በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1723 እንዲሁም 2878 እንደተመላከተው አንደኛ ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር ተያይዞ የሚደረግ ውል በጽሑፍ መደረግ አለበት። ሁለተኛ በጽሑፍ የተደረገው ውል በሚመለከተው አካል ፊት በሕግ በተቀመጠ እና የማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት መደረግ ይጠበቅበታል። በሦስተኛ ደረጃ መመዝገብም ይኖርበታል።

እነዚህ መስፈርቶች በሕጉ የተቀመጡበት ዋና ዓላማ ለተዋዋይ ወገኖች የሕግ ጥበቃ ለመስጠት እንዲቻል ነው። በአዋጅ ቁጥር 922 ላይ ውል እና ማስረጃን በተመለከተ የሰነዶች ማረጋገጫ የተሰጠው ሥልጣን እና ኃላፊነት አለ። በእሱ ፊት የሚደረጉ ማናቸውም ውሎች ታማኝነት እንዳላቸው እና እንደ በቂ ማስረጃ እንደሚቆጠሩ ይገልጻል።

ቤቶች ሲሸጡ በሰነዶች ማረጋገጫ በኩል የሚያልፉ ከሆነ በሕጉ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የሰነዶች ማረጋገጫ ስለሚሸጡት ቤቶች አጠቃላይ ሁኔታ ካጣራ በኋላ ውል ያዋውላል። ስለዚህ አሁን ባለው ሁኔታ ሪል ስቴቶች ገንብተው ከጨረሱ በኋላ ነው ወይ ሽያጩን እያከናወኑት ያለው? የሚል ነጥብ ይነሳል። በሥራ አጋጣሚ ከምናገኛቸው ሁኔታዎች አንጻር ብዙ ጊዜ ሁለት አይነት ውሎች ይደረጋሉ። አንደኛው በፍርድ ቤቶች እና በሰነዶች ማረጋገጫ ያልተደረገ ውል በተለምዶ የመንደር ውል እያልን እንጠራዋለን።

እነዚህ የመንደር ውሎች ከመነሻው በባሕሪያቸው ተዋዋይ ወገኖች እስከተማመኑባቸው ድረስ አስገዳጅ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ አለ። ነገር ግን መተማመን ከሌለ እና መካካድ ከመጣ፣ ‹‹ይህን የመንደር ውል እኔ አልፈጸምኩትም፣ አልፈረምኩትም›› የሚሉ እና ሌሎች

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# ልዩ የምርመራ ዘገባ



# የሪል ስቴቱ ውስጣ ውስጥ...

ከ8ኛው ገጽ የዞረ

ተያያዥ ምክንያቶች ተጠቅሰው አንደኛው ተዋዋይ የማይቀበላቸው ከሆነ በሕጉ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት በመሄድ እርግጥ ይህን ቤት ሲሻሻጡ በሕጉ የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ አሟልተዋል ወይ? ወደሚል ፍርድ ይሄዳል።

በዚህ አግባብ ተዋዋይ ወገኖች እስከተካካዱ ድረስ ይህ ውል እንደረቂቅ ይቆጠራል። ውሉ እንደረቂቅ ከተቆጠረ ደግሞ በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1815 መሠረት ይታያል። በዚህም የተከፈለው ገንዘብ ወደነበረበት እንዲመለስ ይደረጋል። ያ ማለት ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም። ገንዘቡን የከፈለ ሰው ካለ ገንዘቡ ይመለስለታል፤ በተመሳሳይ ያኛው ወገን ያስረከበው ቤትም ሌሎች ንብረቶችም ካሉ ንብረቶቹን በነበሩበት ሁኔታ እንዲረከቡ ተደርጎ ቀድሞ ውል ከመዋዋላቸው በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ነው ፍርድ ቤቱ የሚያደርገው ።

ከዚህ አኳያ በእኛ ሀገር ባለው ሁኔታ ሪል ስቴት አልሚዎች ብዙ ጊዜ ገንብተው ጨርሰው አይሸጡም። ግንባታቸውን የሚያከናውኑት በዋናነት ከገዢዎች በሚሰበሰብ ገንዘብ ነው። ሽያጭ የሚከናወነው የሪል ስቴት አልሚዎች በሚያዘጋጁት የሽያጭ ፎርሞች ወይም ረቂቅ ውሎች ነው።

በዚም አልሚዎች ገዥዎችን በዚህን ያህል ጊዜ ቤት ሠርተን አጠናቀን ልናስረክባችሁ በሚል ስምምነት ያደርጋሉ። በስምምነቱም ገዢዎች የቅድሚያ ክፍያ ይከፍላሉ። የሚፈጸመው ክፍያም ከቤቱ የተወሰነ ወይም ሙሉ ክፍያ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የሽያጭ ውሉ ቤቶች ገና ያልተገነቡ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በሕጉ ከሚቀመጠው መስፈርት መካከል አንዱን አያሟሉም።

### ግንባታው ያልተጠናቀቀን ቤት ማዋዋል በሕግ ያስቀጣል?

ያልተፈጸመን ነገር ሊፈጸም ይችላል ብሎ መዋዋል በዳኞች «ኦብጀክት አፍ ዘ ኮንትራክት» ይባላል። ከዚህ አኳያ አልሚዎች በተዋዋሉበት ጊዜ እንጨርሳለን ብለው ሳይጨርሱ ቀርተው በርካታ ጉዳዮች ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች ይመጣሉ። በተባለው ጊዜ ካላለቀ ገዢዎች ብዙ ጊዜ ችግር ይገጥማቸዋል።

አንዳንድ ጊዜ ከዶላር ምንዛሪ ጋር የሚያያዝ ነው። አብዛኞዎቹ የሪል ስቴት አልሚዎች በዶላር ተመን አውጥተው ሽያጭ ያዋውላሉ። ያ ማለት በዶላር እንዲከፈላቸው ሳይሆን የኮንስትራክሽን ጊዜው ቢራዘም አሁን ባለው የኮንስትራክሽን ወጪ ተጨማሪ ለማስከፈል እንዲያግዛቸው ነው። የቤት ርክክቡን የሚያደርጉበት የዶላር የምንዛሪ ተመንን መሠረት አድርገው ነው። ይህ ማለት የዶላር ምንዛሪ በጨመረ ቁጥር ገዢዎች ለቤቱ የሚከፍሉት ክፍያ እየጨመረባቸው ይሄዳል ማለት ነው።

### ገዢዎች ከውል ጋር በተያያዘ ምን ዓይነት ስህተቶችን ይሠራሉ?

ከውል ጋር ተያይዞ መደረግ የሚገባቸውን የሀገሪቱን ሕጎች ያለመከተል ችግር ነው። የሀገሪቱ ሕግጋቶች ምን ይላሉ? የሚለውን ካልተከተሉ በገዥ እና በሻጭ መካከል የተደረጉ ውሎች በተለያዩ ምክንያቶች ላይፈጸሙ ይችላሉ።

አንድ ተዋዋይ ሁለት ነገሮችን አስቦ መግባት አለበት። አንደኛ የተዋዋልኩት ውል ሕጉን ተከትሎ ሊፈጸም ይችላል? የሚለውን ማየት ያስፈልጋል። ሁለተኛ በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ውል ቀድሞ በተነጋገሩት ስምምነት መሠረት ላይፈጸም የሚችልበትም ዕድል አለ። ስለዚህ በዚህ አግባብ ስምምነቱ ቢፈርስ ሕጉ በቂ ጥበቃ ይሰጠኛል ወይ? የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል።

በቂ ጥበቃ ይሰጠኛል፤ አይሰጠኝም ለማለት ደግሞ መጀመሪያ እንደተዋዋይ ወይም እንደገዢ በሕግ የተቀመጠውን መስፈርት ተከትዬ የፈጸምኩት የውል ተግባር ነው ወይ? የሚለውን መመርመር ይጠይቃል። ከዚህ አንጻር ገዥዎች ክፍተቶች ይታይባቸዋል።

### የውል ጉዳይ በፍትሐ ብሔር ብቻ ወይስ በወንጀልም ይታያል?

ውልን መሠረት ተደርጎ የተፈጸሙ ክሶች ከሆኑ በአብዛኛው በፍትሐብሔር ሕጉ ይታያሉ።። ነገር ግን ውሉን እንደ ሽፋን በመጠቀም ሕጋዊ ያልሆኑ ግብይቶችን ለመፈጸም ከተጠቀሙበት በወንጀል ሊታይ ይችላል። ለምሳሌ ሕዝቡን ለማታለል፣ የሌለውን ነገር እንዳለ አስመስሎ በማጭበርበር ለሰዎቹ ነግሮ እና አስነግሮ ከሆነ በወንጀል ሊታይ ይችላል።

ለምሳሌ ማስታወቂያዎች ሲሠሩ በእውነት ላይ የተመረኮዙ መሆን አለባቸው። ለምሳሌ የሌለን ነገር ያለ አስመስሎ ማስታወቂያ መሥራት እና ሕዝቡ አዎ እነዚህ ሰዎች ያሉት እውነት ነው ብሎ ተቀብሎ በዚያ አግባብ ገንዘቡን ካወጣ በኋላ ያ የተባለው ነገር ባይኖር የተታለሉት ሰዎች ገንዘባቸውን ለማስመለስ ጥያቄ ማንሳት ይችላሉ፤ በወንጀል ሊያስከስስም ይችላል። ለምሳሌ የሌለውን መሬት ይህ ይዞታ የኔ ነው፤ በዚህ ቤት ገንብቼ ልሸጥ ነው ብሎ ሰዎችን አታልሎ ገንዘብ ቢቀበል በወንጀል ያስጠይቃል።

### ሪል ስቴትን ለመዳኘት ያለው የዳኞች ፈተናዎች

ሪል ስቴትን ብቻ ለመዳኘት የሚያስችሉ ሕጎች የሉንም። ዘርፉን የምንዳኘው ሌሎች ሕጎችን መሠረት በማድረግ ነው። ይሁን እንጂ ያሉንን ሕጎች መሠረት አድርገን ምን ያህሎቻችን ውል እየተዋዋልን ነው? የሚለውም ሌላ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። ከሪል ስቴት ጋር ይሁን ከሪል ስቴት ውጭ ያሉ ነገሮችን ስንገበያይ በሕጉ መሠረት አንድ የሽያጭ ውል ሲደረግ ማሟላት ያለባቸውን ነገሮች አሉ።

ከእነዚህ መካከል ገዥ እና ሻጭ የሚያደርጓቸው የግብይት ውሎች በጽሑፍ መደረግ አለባቸው የሚለው አንደኛው ነው። ከጽሑፍ በተጨማሪም ውሉ በምስክሮች እና ሕጉ በሚፈቅደው ውል አዋዋይ ፊት መሆንም አለበት። ነገር ግን አብዛኛዎቹ የሪል ስቴት ገዢዎች ይህን አያደርጉም። በዚህም ከሪል ስቴት ጋር የተገናኙ ክሶችን ለመዳኘት ፈተና ነው።

### ጉዳት የደረሰባቸው ግለሰቦች

ጉዳት የደረሰባቸውን ግለሰቦች እና የሽያጭ ባለሙያዎችን ለማግኘት የምርመራ ቡድኑ በርካታ መስፈርቶችን ተጠቅሟል። ከእነዚህም መካከል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሄድ በተደጋጋሚ አቤቱታ የሚቀርብበት ሪል ስቴት የቱ ነው? የሚለውን የልየታ ሥራ አከናውኗል። ይህን ከአከናወነ በኋላ ተጎጂዎችን እና የሽያጭ ባለሙያዎችን መርጧል።

ከተጎጂ አንጻር ጉዳያቸው በፍርድ ቤት የታየላቸውን ግለሰቦች በመምረጥ በዘገባው ለማካተት ተሞክሯል። በዘገባው ያነጋገርናቸው ተጎጂዎች ለከፍተኛ ሥነልቦናዊ ችግር ተጋልጠው አግኝተናቸዋል። ቃለመጠይቁን ስናደርግም ስማቸው እንዳይገለጽ አበክረው ጠይቀውናል። ማሳያ 1. ለዘገባው ሲባል ተበዳይን አቶ መታገስ ከፈለኝ ብለናቸዋል።

እንደ አቶ መታገስ ገለጻ፤ የሪል ስቴት አልሚው ባለሦስት መኝታ ቤት በ18 ወራት ሠርቶ ሊያስረክባቸው እና ሠርቶ ሲጨርስ ገዥዎችም ሙሉ ክፍያ ሊፈጽሙ ነበር። የሪል ስቴት አልሚውም በውሉ መሠረት የግንባታውን ሌት ተቀን ብሎ በማከናወን 60 በመቶ አደረሰው። ግንባታው 60 በመቶ እስከሚደርስ ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ነበር። የቤቱ ግንባታ 60 በመቶ ላይ ሲደርስ አልሚው ገዢዎችን የቤቱን ዋጋ መቶ በመቶ እንዲከፍሉ ጠየቀ። ገዥዎችም ግንባታው 60 በመቶ እስከሚደርስ ያለውን ሂደት በማየት የተጠየቁትን ገንዘብ ለመክፈል ተስማሙ። ለዚህም ከዛሬ 12 ዓመት በፊት አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር ከፈሉ።

ሙሉ ክፍያውን ያገኘው የሪል ስቴት ከአልሚው ሙሉ ገንዘቡን ማግኘቱን ሲያረጋግጥ ግንባታውን ሙሉ በሙሉ አቁሞ ጠፋ። በዚህ የተጨነቁት ገዥዎች ከዛሬ ነገ ግንባታው ይጀምራል ብለው ቢጠብቁም አልሚው የውሃ ሽታ ሆነ። በመጨረሻም ተስፋ በመቁረጥ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወሰዱ። ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን ለአምስት ዓመታት ሲያይ ቆይቶ 60 በመቶ የደረሰውን ቤት ገዥዎች እንዲወስዱ አዘዘ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኮንትራክተሩ ደግሞ ሪል ስቴቱን የገነባበትን ገንዘብ ከአልሚው አልተቀበለም ነበርና "ገንዘቤ ይሰጠኝ" ሲል ለፍርድ ቤት አመለከተ። በዚህም ፍርድ ቤቱ አልሚውን እና ኮንትራክተሩን ሲያከራክር ቆይቶ በመጨረሻም የተገነባው ቤት ማለትም 60 በመቶ የደረሰው ሰዎች የገዙትን ቤት እንዲሸጥ እና ለግንባታ ያወጣውን ገንዘብ እንዲወስድ ፈረደለት።

በዚህም ወቅት አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር ከፍለው የነበሩ ገዥዎች ስለጉዳዩ ሰሙ። ዘግይተውም ቢሆን ንብረታቸውን ሊያጡ ከጫፍ መድረሳቸውን ተገነዘቡ። ይህን ተከትሎ ጉዳዩን ወደ ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት ወሰዱ። ኮንትራክተሩ እና ገዥዎች ለሦስት ዓመታት ተከራክረው በመጨረሻም ፍርድ ቤቱ "ግንባታው 60 በመቶ የደረሰው ቤት ለገዥዎች ይገባቸዋል" ሲል ወሰነ። በዚህም ገዥዎች በ18 ወራት ውስጥ ቤት ሊያገኙ የተዋዋሉ ቢሆንም ስምንት ዓመታት ቤት ሳያገኙ ፍርድ ቤት ለፍርድ ቤት እየተንከራተቱ እንዲሳልፉ ሆነ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አልሚው እንደገና "45 ሚሊዮን ብር ክፈሉኝ ወይም የአረንጓዴ ልማት ቦታውን እና ለተሽከርካሪ ማቆሚያ የተዘጋጀውን ቦታ ስጡኝና ቤቱን አጠናቅቄ ልስጣችሁ" ብሎ መጣ። በዚህም በሻጭ እና በገዥ መካከል እንደገና እሰጥአገባ ተጀመረ። ነገር ግን ገዥዎች አልሚውን እንደማያምኑት፤ የአረንጓዴ ልማት ቦታውን እና ለተሽከርካሪ ማቆሚያ የተዘጋጀውን ቦታ እንደማይሰጡት በመንገር መለሱት። ይህም ሆኖ ገዥዎች ያልተጠናቀቀ ቤታቸውን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ከሦስት ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ለማውጣት ተገደዋል።

በዚህ ታሪክ ላይ በርካታ ነገሮች ልብ ሊባሉ ይገባል! አንደኛ አልሚው ቤቱን ጨርሶ ሊያስረክብ የነበረው በ18 ወራት ውስጥ ነበር። ነገር ግን ያ ሳይሆን ቀርቶ ገዢዎች ቤታቸውን ሳያገኙ 12 ዓመት አሳለፉ፤ ሁለተኛ በአንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር ቤት ሊያገኙ የነበሩ ሰዎች በአልሚው ችግር ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ እንዲያወጡ ተገደዱ፤ ትልቁ እና ዋናው ችግር ደግሞ በተፈጠረው ውዝግብ ሳቢያ በገዥዎች ቤተሰቦች ላይ ከፍተኛ የሆነ የሕይወት ምስቅልቅል ተፈጥሯል። በደረሰባቸው ሥነ-ልቦናዊ ጉዳት እና በችግር እስከመሞት የደረሱም አሉ።

እንደተወካዩ ገለጻ፤ ድክመቱ ያለው መንግሥት ጋር ነው። ለምሳሌ መንግሥት ከብሔራዊ ባንክ ተቆጣጣሪ አካል አቋሞ ባንኮችን ይቆጣጠራል። ለሌሎች መሥሪያ ቤቶችም እንዲሁ፤ ከሪል ስቴት ጋር በተያያዘ መንግሥት ሕግ አውጥቶ ከመቆጣጠር አንጻር ክፍተቶች ይታዩበታል። በዚህም በርካታ ሰዎችም ለከፋ የሕይወት ምስቅልቅል ከመዳረጋቸውም ባለፈ ሕይወታቸውን እስከማጣትም ደርሰዋል። መንግሥት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የማያዳግም እልባት ሊያስገኝ የሚችል ሕግ እና መመሪያ እንዲያወጣለት ጠይቀዋል።

### የሽያጭ ባለሙያዎች ስለሪል ስቴት ሽያጭ

የምርመራ ቡድኑ በአንድ ሪል ስቴት ተቀጥረው ይሠሩ የነበሩ የቀድሞ ሽያጭ ባለሙያዎችን በመምረጥ ለዚህ ዝግጅት አቅርቧል። የቀድሞ የሽያጭ ባለሙያዎችን ለማነጋገር የመረጥንበት ዋና ምክንያት አሁን ላይ በሽያጭ ሙያ በድርጅቱ ተቀጥረው የሚሠሩ ከሆነ በፍርሃት ወይም በሌላ ምክንያት ሙሉ መረጃ ሊሰጡን አይችሉም ከሚል ሀሳብ ነው። የቀድሞ የአያት ሪል ስቴት የሽያጭ ባለሙያዎች የሚከተለውን ብለውናል፡-

ይህ ሪል ስቴት ለሽያጭ ሠራተኞቹ ኮሚሽን እንኳን ለመክፈል አይፈልግም። ለሽያጭ ባለሙያዎች ኮሚሽን የሚከፍለው በድርጅቱ የውስጥ መመሪያ ነበር። የተሸጠው ቤት በግንባታ ላይ ያለ በመሆኑ እና ለገዢ በተባለው ጊዜ ተገንብቶ ስለማይሰጥ ገዢ ክፍያውን በአንድ ጊዜ አይፈጽምም። በመሆኑም ድርጅቱ ለሽያጭ ሠራተኞቹ መክፈል የነበረበትን የኮሚሽን ክፍያ አይፈጽምም በዚህም በተደጋጋሚ ከሽያጭ ሠራተኞች ጋር ፀብ ውስጥ ይገባል። አንዳንድ ጊዜም ፀቡ አድጎ ፍርድ ቤት ይደርሳል።

ሪል ስቴቱ በጊዜው ሠርቶ ባለማጠናቀቁ የሠራተኞች ኮሚሽን በጊዜው አይከፈልም። በጊዜው ኮሚሽን ያልተከፈለው ሠራተኛ ለመኖር ሲል ከሞራል ውጭ የሆነ ሥራ ሊሠራ ይችላል። ከዚህ ቀደም ውል የተዋዋሉ ገዢዎች ቤት እንዳላገኙ እያወቀ የኮሚሽን ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ሌላ ተዋዋይ ለማምጣት ይጥራል።

ድርጅቱ ከ10 እስከ 15 በመቶ ቅድመ ክፍያ ያስከፍላል። ደንበኞች በተወሰነ ጊዜ ተሠርቶ ይሰጣችኋል ብሎ በሽያጭ ባለሙያ አግባቢነት ግዥ ከተፈጸመ በኋላ ቤታቸውን በጊዜው ሳያገኙ ሲቀሩ ከማርኬቲንግ ባለሙያው ጋር እስከመጣላት ይደርሳሉ። የሽያጭ ባለሙያውም ሥራውን ለቆ እስከመጥፋት የሚደርስበት ጊዜ አለ።

የሽያጭ ባለሙያው ቤት ሸጦ ኮሚሽን ለማግኘት የማይወጣበት እና የማይወርድበት ቦታ፤ የማይቧጥጠው ተራራ የለም። ያም ሆኖ በአልሚው ኮሚሽኑ በቅጡ አይከፈለውም። ይህ ማለት ግን ሁሉም ማለት አይደለ። በጣም ጥቂት፤ በጣት የሚቆጠሩ የሪል ስቴት አልሚዎች ሠራተኛው ሥራ ቢለቅም እንኳን ኮሚሽኑን ጠርተው የሚከፍሉ አሉ። አብዛኛዎቹ ግን የሽያጭ ባለሙያው ተንከራቶ ያመጣውን ኮሚሽን አይከፍሉም። ይህ ደግሞ ሕመሙ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ያስረዳሉ።

### በተደጋጋሚ ፍርድ ቤት ክስ የሚቀርብበት ሪል ስቴት የቱ ነው?

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከሪል ስቴት ጋር በተገናኘ ሰፋ ያለ ምርመራ አድርጎ ነበር። በዚህ ምርመራ በርካታ ጉዳዮችን ከዳሰሰ በኋላ በተለይም በኢትዮጵያ የፌዴራል ፍርድ ቤት በርካታ ጊዜ ክስ የቀረበበት ሪል ስቴት ማን ነው? የሚለውን ለማየት ሞክሯል። በዚህም መሰረት ለበርካታ ጊዜያት በተደጋጋሚ በቤት ገዥዎች ከተከሰሱት፤ አክሰስ እና አያት ሪል ስቴት አልሚዎች በቀዳሚነት ሲገኙ ኒው ላይን ሪልስቴት ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ተቀምጧል።

# የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ ወደ ጎተራ

**ኢያሱ መሰለ**

የግብርና ሥራን ውጤታማ ሊያደርጉ ከሚችሉ የሥራ ሂደቶች ውስጥ አንዱ የድህረ ምርት አሰባሰብ ነው። በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች የሚገኙ አብዛኛዎቹ አርሶ አደሮች በተለይም ከጥቅምት እስከ ጥር ባሉት ወራት የመኸሩን ምርታቸውን ወደ ጎተራ ያስገባሉ። ኢትዮጵያ ከፍተኛ የግብርና ምርት የምታገኘውም በዚሁ የመኸር ወቅት ነው። በምርት መሰብሰቡ ሂደት በሚያጋጥሙ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮችም ከፍተኛ የምርት ብክነት ሊፈጠር እንደሚችል ጥናቶች ያመላክታሉ።

ከሰሞኑ "ከረሀብ ነፃ ዓለም" ዓለም አቀፍ ጉባዔ በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደበት ወቅት የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ መለሰ መኮንን (ዶ/ር) የጥናት ውጤቶችን መሠረት አድርገው ሲያብራሩ በኢትዮጵያ በየዓመቱ 46 ሚሊዮን ዜጎችን መመገብ የሚችል ምርት በድህረ ምርት ሂደት ይባክናል። የድህረ ምርት ብክነት የሚደርሰው ከምርት መሰብሰብ ጀምሮ እስከ መጠቀም ባለው ሂደት እንደሆነ ተናግረው ይህም በዓመት ከ12 ሚሊዮን ቶን ምርት በላይ ይገመታል ብለዋል።

እንደ ጥናቱ ማብራሪያ ከረሀብ ነፃ ዓለም ለመፍጠር ሲታሰብ በሀገርም ይሁን በዓለም ደረጃ የድህረ ምርት ብክነትን መቀነስ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ዶክተር መለሰ በድህረ ምርት የሚባክን ምርትን ማስቀረትና መቀነስ ቢቻል በሀገር ደረጃ የምግብ ዋስትና ያልተረጋገጠለት ወይም የዕለት ቀለብ የሚሰፈርለት ዜጋ እንደማይኖር፤ በሀገርና በቤተሰብ ደረጃም የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እንደሚቻል ያረጋግጣሉ።

ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ፣ የአንበጣ ወረርሽኝ፣ ግጭት ወይም ጦርነት፣ ጥንቃቄ የጎደለው የምርት አሰባሰብ እና ሌሎችም ጉዳዮች ለድህረ ምርት ብክነት በምክንያትነት ልንጠቅሳቸው የሚችሉ ናቸው። በግብርና ሥራ ውስጥ ላብን ጠብ አድርጎ፣ አቅምን እና ቴክኖሎጂን አሟጦ በመጠቀም አዝመራን ቶሎ ሰብስቦ ወደ ጎተራ ማስገባት ያስፈልጋል።

የደረሰ ሰብል እንዳይባክን ከፍተኛ ጥንቃቄና አጣዳፊ ሥራ ሰርቶ በሰዓቱ ወደ ጎተራ ማስገባት ቢቻል ምርታማነት የበለጠ ያድጋል፤ በምግብ ራስን የመቻል ህልማችንም እውን ይሆናል።

ከዚህ አንጻር ለአርሶ አደሮቻችን ግንዛቤ የማስጨበጡ ጉዳይ ጊዜ የሚሰጠው ሊሆን አይገባም። ሌላው ቀርቶ አርሶ አደሮቻችን የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በየጊዜው የሚሰጣቸውን ወቅታዊ መረጃዎች እየተከታተሉ ለሥራቸው በሚያግዝ መልኩ ጥቅም ላይ የማዋል ልምዳቸው አናሳ ነው ተብሎ የሚገለጽ ብቻ ሳይሆን ከዚያም የወረደ ነው።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በመኸር አዝመራ ከፍተኛ ሄክታር መሬት በዘር የሸፈነችው በዘንድሮው የመኸር ወቅት መሆኑን የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) ከሰሞኑ መግለጻቸው ይታወሳል። የግብርና ሚኒስቴር መረጃም በዘንድሮው ዓመት የግብርናው ዘርፍ 6 ነጥብ 1 በመቶ እድገት የሚያስመዘግብ መሆኑን አመላክቷል።

ይህ ግምት እውን የሚሆነው እያንዳንዱ አርሶ አደርም ይሁን የሚመለከተው ባለድርሻ አካል ተስፋ የተጣለበትን መስክ ላይ ያለ ሰብል ለብክነት ተጋላጭ ሳይሆን ታጭዶና ተወቅቶ ለጎተራ እንዲበቃ ማድረግ ሲችል ነው።

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ከሰሞኑ በሰጠው የአየር ትንበያ መረጃ የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ በመካከለኛው፣ በምሥራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከጥቅምት 7 እስከ ኅዳር 23 ቀን 2017 ዓ.ም ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ጠቁሟል። የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑት በነዚህ አካባቢዎች ሊኖር የሚችለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት በየጣልቃው የሚኖሩትን ደረቃማ ቀናት በመጠቀም የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ መሰብሰብ እንዲችሉም አሳስቧል።

የሀገሪቱ የግብርና ምርታማነት እያደገ የመጣው በተለይም መንግሥት ከዓመታት በፊት የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ከአምስቱ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዘርፎች

**እንደ ግብርና ሚኒስቴር መረጃ በ2016/17 ምርት ዘመን የመኸር እርሻ በእቅድ ከተያዘው ውስጥ 20 ነጥብ 5 ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል። ከዚህም 608 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚገኝ ይጠበቃል**

አንዱና ዋነኛው አድርጎ በትኩረት እየሠራ በመሆኑ ነው። የከተማ ግብርና፣ የበጋ ስንዴ፣ የሌማት ትሩፋትን የመሰሉ ንቅናቄዎች ለግብርናው ዘርፍ ምርታማነት ጉልህ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ያሉ እንግዳ የሥራ ባሕሎቻችን ናቸው። አርሶ አደሩ የግብርና ፓኬጆችን እንዲጠቀም፣ የኩታ ገጠምና የሜካናይዜሽን አስተራረስ ዘዴን እንዲከተል መደረጉም ለምርታማነቱ አስተዋጽኦ እንዳበረከተለት የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

እንደ ግብርና ሚኒስቴር መረጃ በ2016/17 ምርት ዘመን የመኸር እርሻ በእቅድ ከተያዘው ውስጥ 20 ነጥብ 5 ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል። ከዚህም 608 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚገኝ ይጠበቃል። ከ15 ሚሊዮን ሄክታር በላይ በባሕላዊ መንገድ፤ ከ5 ሚሊዮን ሄክታር በላይ ደግሞ በሜካናይዝሽን ወይም በትራክተር ታርሷል። የግብርናው ዘርፍ መነቃቃት በምርት እድገት ላይ የፈጠረው ለውጥ የሚደነቅ ቢሆንም በብዙ ድካምና ልፋት ለጥሩ ፍሬ የበቃውን ሰብል ለብክነት አጋላጭ ከሆኑ ነገሮች ጠብቆ ለጎተራ የማብቃቱ ጉዳይ ግን ገና ብዙ ሊሠራበት የሚገባ ነው።

የሀገራችን ግብርና ዛሬም ድረስ ከኋላ ቀር አሠራርና ከበሬ ትከሻ ያልተላቀቀ ነው፤ በዘንድሮው መኸር ወቅት በትራክተር የታረሰው መሬታችንም ከአንድ አራተኛ የሚበልጥ አይደለም። ግብርናችን ከዚህም በላይ መዘመን ቢችል የምርታማነታችን መጠን የቱን ያህል ሊያድግ እንደሚችል የዘንድሮው ውጤት ምስክር ነው። በግብርና ሥራ ላይ የተጀመረውን ንቅናቄ አጠናክሮ መቀጠል ቢቻልና አርሶ አደሩን ከዚህም በላይ መደገፍ ቢቻል በምግብ ራስን የመቻል ህልማችንን እውን አድርገን ቀሪ ምርታችንን ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚያስችል ትልቅ አቅም እንዳለን የተረዳንበት አጋጣሚ ነው።

ከሰሞኑ "ከረሃብ ነፃ ዓለም" ዓለም አቀፍ ጉባዔ በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባደረጉት ንግግር የምርጥ ዘር አቅርቦት እጥረትና የግብርና ግብዓት አቅርቦት እጥረት ፈተና ቢሆኑም ኢትዮጵያ ባለፉት ስድስት ዓመታት ረሀብን በመዋጋት ረገድ ውጤት አምጥታለች።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ኢትዮጵያ በግብርና ማሻሻያ ላይ ትኩረት ሰጥታ መሥራቷንና ድርቅን መቋቋም የሚችሉ ሰብሎችን በመዝራት ምርታማነትን ማሳደግ መቻሏንም ተናግረዋል።

ዓለምን የተፈታተኑ ታላላቅ ችግሮች ቢኖሩም ጥረትን በእጥፍ በመጨመር፣ ፈጠራ የታከለባቸውን ሥራዎች በመተግበርና ዘመናዊ የግብርና ሥራን በመከተል ፈተናዎችን ተቋቁሞ ምርታማነትን ማሳደግ ስለመቻሉም ጠቅሰዋል። በርግጥም ኢትዮጵያ ከተረጂነት ወጥታ ራሷን ለመቻል የምታደርገው ጥረት ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን ለማወቅ የዛሬ ሰላሳና አርባ ዓመታት ጥቂት ሕዝብ ይዛ እጇን ለምጽዋት የዘረጋችበትን እና አሁን እጆቿን ሥራ ላይ አውላ ከ120 ሚሊዮን በላይ ዜጎቿን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እያደረገች ያለውን ጥረት አይቶ መረዳት ይቻላል። ይህን እኛ ልብ ላንለው እንችል ይሆናል፤ ነገር ግን ዓለም አይቶ ምስክርነት የሰጠበት ሀቅ ነው።

«ከረሃብ ነፃ ዓለም» ጉባኤ ላይ የተገኙት የአፍሪካ ህብረት ሊቀ መንበር ሙሳ ፋቂ በንግግራቸው ያረጋገጡትም ይህንኑ ነው። አፍሪካ የተፈጥሮ ሀብት ብዝሀነት ያላት አህጉር ብትሆንም አሁንም ድረስ የምግብ ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ አልቻለችም ያሉት ሙሳ ፋቂ ረሀብን ከአፍሪካ ምድር የማጥፋት ጉዳይ የነገ ሳይሆን የዛሬ ተጨባጭ ሥራ ሊሆን ይገባል ነው ያሉት። የአፍሪካን የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ ጥራት ያለው የግብርና ሥራ በመተግበር ምርታማነትን ማስፋፋት ያስፈልጋል፤ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ እየተገበረች ያለችው ሞዴል የግብርና ትራንስፎርሜሽን ሥራ የሚበረታታ እና ለሌሎች ምሳሌ መሆን የሚችል ነው ሲሉ አወድሰዋል።

ሞዴል የግብርና ሽግግር ምርት ማምረትን ብቻ ሳይሆን የምርት ብክነት መቀነስንም የሚመለከት ነው። ሰብሎች በጥሩ ክትትልና እንክብካቤ ተይዘው ፍሬያማ ከሆኑ በኋላ ታጭደውና ተወቅተው ወደ ጎተራ በሚገቡበት በመጨረሻው ሰዓት በሚፈጠሩ አንዳንድ ሁኔታዎች ከፍተኛ ብክነት ይፈጠራል። ብዙውን ጊዜ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እና ጥንቃቄ የጎደለው የምርት አሰባሰብ ሂደት ለድህረ ምርት ብክነት በምክንያነት ቢጠቀሱም የአንበጣ ወረርሽኝ፣ ጦርነትና ጦርነትን ተከትሎ የሚከሰት ስደት በምርት መሰብሰብ ሂደት ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ተጨማሪ ችግሮች ናቸው።

ከዚህ አንጻር ከሀገራችን ተሞክሮ ተነስተን ብዙ ማሳያዎችን መጥቀስ እንችላለን። ለምሳሌ፤ ከሶስትና አራት ዓመታት በፊት በሀገራችን የተከሰተው የአንበጣ ወረርሽኝ በደረሱ ሰብሎች ላይ ምን ያህል አደጋ አስከትሎ እንደነበር የተመለከትነው ሀቅ ነው። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የነበረው የእርስ በእርስ ግጭት የደረሱ ሰብሎች በሥርዓት ተሰብስበው እንዳይገቡና ምርታማነታችን በሚፈለገው ደረጃ ከፍ እንዳይል ተጽዕኖ መፍጠሩም የሚታወስ ነው። ዛሬም በአንዳንድ የሀገራችን አካባቢዎች የሚስተዋሉት ግጭቶች አርሶ አደሩ ተረጋግቶ ሥራውን እንዳይሠራ በማድረግ በምርታማነታችን ላይ አሉታዊ ጥላ ማጥላታቸውን እያየን ነው። ግብርናችን እነዚህን ሁሉ ችግሮች ተቋቁሞ ምርታማ መሆኑም የሚያስደንቅ ነው።

የምርት ብክነትን በየአንዳንዱ አርሶ አደር ወይም በግለሰብ ደረጃ ስንመለከተው ትንሽ ሊመስለን ይችላል፤ ነገር ግን በምርት መሰብሰብ ሂደት እያንዳንዱ አርሶ አደር ላይ የሚፈጠረው የምርት ብክነት ሲደማማር ከፍተኛ የሆነ ሀገራዊ ጉዳት የሚያስከትል እንደሆነ ቀደም ባለው የጥናት ውጤት መረዳት ችለናል። አርሶ አደሩ በብዙ ኩንታል የተመናቸውና በብዙ ብር የለካቸው በቁም ያሉት ሰብሎች፤ ታጭደው ወደ ጎተራ ከመግባታቸው በፊት በተለያዩ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች ምክንያት የመባከናቸው ጉዳይ መፍትሔ ካላገኘ ምንጊዜም ቢሆን ምርታማነታችን ላይ ተጽዕኖ መፍጠሩ የማይቀር ነው።

ከሰሞኑ እየተመለከትነው ያለነው ደመናማ የአየር ፀባይም ምርታማነታችንን ጥያቄ ውስጥ እንዳይከተው ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ከቀበሌ እስከ ፌዴራል መንግሥት ያሉ አመራሮችም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ሕዝብን በማንቀሳቀስ የደረሱ ሰብሎች በወጉ ታጭደውና ተወቅተው ወደ ጎተራ እንዲገቡ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ከሳምንታት በፊት በቆላማና ከፊል ደጋማ አካባቢዎች የመኸር አዝመራው እየተሰበሰበ እንደሚገኝ እና እስከዚያን ጊዜ ድረስ በአምስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የተዘራ ሰብል መሰብሰቡን የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ ዶ/ር መግለጻቸው ይታወሳል። በአሁኑ ሰዓትም የዚህ መረጃ አህዝ በወቅቱ ከተጠቀሰው በላይ ከፍ ሊል እንደሚችል ይታመናል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ በደጋና በአብዛኛው ወይና ደጋ አካባቢዎችም የሰብል አዝመራው በጣም ጥሩ ቁመና ላይ ይገኛል፡ በቀጣይም አዝመራን የመሰብሰቡ ሂደት ተጠናክሮ የሚቀጥል እንደሚሆንና ይህም ለአምራቹ ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁሉንም ተሳትፎና ጥረት የሚጠይቅ መሆን እንደሚገባው አሳስበዋል።

ኢትዮጵያ ያለማችውን ከፍተኛ ምርት ሙሉ ለሙሉ እውን ማድረግ የምትችለውና ምርትን ከብክነት መታደግ የሚቻለው ክረምቱን ሁሉ ርብርብ ሲደረግበት የነበረውን ሰብል በወቅቱና በጥራት መሰብሰብ ሲቻል እንደሆነም አስምረውበታል።

በየደረጃው ያሉ የመንግሥት አመራሮች፣ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ሁሉንም የሰብል መሰብሰቢያ ቴክኖሎጂዎች እንዲጠቀሙና ምቹ ሁኔታዎችን እንዲፈጥሩ፤ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ተማሪዎች እንዲሁም የመንግሥት ፀጥታ አካላት በልዩ ሁኔታ ድጋፍ እንዲያደርጉም ጥሪ ማቅረባቸው ይታወሳል።

ይነስም፤ ይብዛም የኢትዮጵያን ሕዝብ እየመገበ ዘመናትን ያሻገረው የአርሶ አደሩ ብርቱ ክንድ ነው። የሕዝብ ቁጥር እያደገ በመጣ ቁጥር የማምረት አቅማችንም በዚያው ልክ ማደግ ካልቻለ ኑሯችን ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ የመሆኑ ጉዳይ የማይቀር ነው። በልመና እና በርዳታ ስንዴ የኖርብትን ዘመን ታሪክ ለማድረግ መንግሥት በግብርናው ዘርፍ የወሰዳቸው ርምጃዎች አስደናቂ ለውጦች ተመዝግበውበታል። ምርታማነታችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቶ ከዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት ከነበረው ሕዝብ በእጥፍ ያደገውን ሕዝባችንን እየመገበ ነው። ይህ ቀጣይነት እንዲኖረው እያንዳንዱ ዜጋ ግብርናውን ውጤታማ ለማድረግ የተቀረጹ አዳዲስ አሠራሮችን ማለትም፤ የከተማ ግብርናን፣ የሌማት ትሩፋትን፣ የበጋ ስንዴን የመሳሰሉ ፕሮግራሞችን ከመተግበር ባለፈ አርሶ አደሩን በሁሉም ዘርፍ መደገፍና ማገዝ ይጠበቅበታል።

አሁንም የደረሱ ሰብሎች ለብክነት እንዳይዳረጉና የተገመተውን ምርት ወደ ጎተራ አስገብተን በምግብ ራሳችንን የመቻል ህልማችንን እውን እንድናደርግ አርሶ አደሮቻችን እንደ ጅጊ ፣ ወንፈል እና ደቦን የመሳሰሉ የመረዳዳት ባሕሎቻችንን ተጠቅመው አዝመራቸውን መሰብሰባቸው ሳይዘነጋ ሁላችንም በያለንበት ቦታ ሁሉ ከአርሶ አደሩ ጎን ቆመን የደረሱ ሰብሎችን የመሰብሰብ የውዴታ ግዴታችንን ልንወጣ ይገባል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ህልምን የመከተል ውጤት- የወጣት ሥራ ፈጣሪዋ ስኬት

አመሰወርቅ ከበደ

ነገዋን ብርሃን ለማድረግ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ትታትራለች። እይታዋን ከፊቷ የሚታያት ብሩህ ቀን ላይ አድርጋ ተስፋ መቁረጥን «ዞር በል!» ብላዋለች። ምክንያቱን ነገን በስኬት እንድትፈካ ዛሬን ተስፋ ማድረግ የግድ ይላታል። ለዚህ ደግሞ ጠንክራ መሥራት እንዳለባት ታውቃለች።

በልጅነቷ በእግሯ ላይ በገጠማት አደጋ የአካል ጉዳት አጋጥሟት ነበር። በህክምና ቀዶ ጥገና ብታደርግም አሁንም ረጅም መንገድ ስትራመድ የህመም ስሜቱ አብሯት ዘልቋል። በዚህ ፈተና ግን አልተሰበረችም፤ የአካል ጉዳቷ የአዕምሮ ስብራት ሳይሆንባት፤ የ"ይቻላል" መንፈስ በልቧ ተጭሮ ይበልጥ አጠነከራት እንጂ ተስፋ አላስቆረጣትም። ፈተና ከሚያጠነክራቸው እንጂ ከሚሰብራቸው ወገን አይደለችም።

ትናንት በተስፋ መነፅር አሻግራ ወዳየችው ታላቁ መዳረሻዋ ለመድረስ ዋናውን መንገድ አግኝታ ጉዞ ጀምራለች። የራሴ የምትለውን ሥራ ከመሥራትም ባለፈ፤ በተወሰነ ደረጃ ሌሎችን ቀጥራ ታሰራለች። ለዚህ ያበቃት ወደኋላ ከሚጎትታት እኩይ ሃሳብ ይልቅ ተስፋና ጥንካሬን የሚያጎናጽፏትን የመበርታት እሳቤ መርጣለች። ለዚህ ነው የዝግጅት ክፍላችን የዛሬው የሴቶች ገጽ እንግዳ ሊያደርጋት የወደደው።

ወጣት ብርሃን ቀነአ ትባላለች፤ የተለያዩ የቆዳ ቦርሳዎች፣ ጫማዎች እና ሌሎች በቆዳ የሚሰሩ እቃዎችን ታመርታለች። የተወለደችው ወሊሶ አካባቢ ቢሆንም፤ በአዲስ አበባ ከተማ ከዘመዶቿ ቤት ነው ያደገችው። የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የወሰደች ቢሆንም፤ እንዳለመታደል ሆኖ ዩኒቨርሲቲ ሊያስገባት የሚችል ውጤት አላመጣችም። በዚህ ምክንያት ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ገብታ መማር የግድ አላት። በዙሪያዋ ያሉ ሰዎች ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን ብትማር የተሻለ እንደሚሆን ቢመክሯትም የልቧን ፍላጎት ለማስቀደም ግን አላመነታችም።

"የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ምኒልክ ትምህርት ቤት ነበር የተማርኩት። እንዳጋጣሚ ሆኖ የማትሪክ ውጤት አልመጣልኝም» የምትለው ወጣት ብርሃን፤ ወዲያው ቴክኒክና ሙያ ገብታ ለመማር እንደወሰነች ትናገራለች። ነገር ግን ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቱ በቆዳ ዘርፍ እንደሚያስተምር አታውቅም ነበር። ለምዝገባ ስትሄድ የስልጠና ዓይነቶችን አሳይተው ሲያስመርጧት ግን ሥልጠናው መኖሩን ተረዳች። በቆዳ ዘርፍ ለመማር ብትመርጥም መምህራኑ ግን ውጤቷ ጥሩ ስለነበረ ማኔጅመንት፣ አካውንቲንግና ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች እንድትመርጥ ስለፈለጉ ምክር ሰጧት። ነገር ግን እሷ የቤተሰቦቿን ሃሳብ ነበር ለመቀበል የፈለገችው። በቆዳ የሙያው ዘርፍ እንድትማር የሰጧትን ሃሳብ ተቀብላ ለመቀጥል ወሰነች።

የሥራ ፈጣሪዋ ወጣት ብርሃን በቴክኒክና ሙያ በደረጃ አራት በቀን ፕሮግራም እየተማረች በማታ ፕሮግራም ደግሞ አካውንቲንግ በዲፕሎማ አጠናቀቀች። ከሙያ በተጨማሪ አካውንቲንግ መማሯ በንግድ ሥራዋ ላይ የሂሳብ ሥራዎችን በራሷ እንድትሰራ እንደረዳት ትናገራለች።

ወደ ሥራው እንዴት እንደገባች የምትናገረው ወጣት ብርሃን፤ ተመርቃ ከወጣች በኋላ ተቀጥራ መሥራት ብትጀምርም የምታገኘው ደመወዝ ዝቅተኛ ስለነበር ግራ መጋባት ውስጥ ነበረች። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለች ነበር በግሏ ለመሥራት የወሰነችው።

"የሥራውን ሂደት ጀመርኩና ለመንግሥት አካላት የመሥሪያ ቦታ እንዲሰጠኝ ጥያቄ አቀረብኩኝ» በማለት እንዴት ወደ ሥራው እንደገባች የምትናገረው ወጣት ብርሃን፤ ጥያቄዋ በተማረችበት የትምህርት ዘርፍ ለመሥራት እንደነበር ተናገራለች። የተግባር ፈተናውን አልፋ ስለነበርና የትምህርት ውጤቷም ጥሩ በመሆኑ ጥያቄዋ ተቀባይነት እንዳገኘ ትናገራለች። እነሱ ከተቀበሏት በኋላ ለማሽን መግዣ፣ የቆዳ መቁረጫ እና የቆዳ ጥሬ እቃ ለመግዛት ገንዘብ ስላጠራት ቀጥታ ወደ ሥራው ለመግባት ጊዜ ወስዶባት ነበር።

ምንም እንኳን የመሥሪያ እቃዎችን ለመግዛት የገንዘብ ችግር ቢገጥማትም፤ ለተስፋ መቁረጥ ምክንያት እንዲሆናት አልፈቀደችም። ገንዘብ ለማግኘት የአበዳሪ ተቋማትን በር ማንኳኳት ጀመረች። እነሱም ፊት ሳይነሷት የሚያስፈልጋትን ብር ሰጥተዋት አስፈላጊ እቃዎችን መግዛት ቻለች።

"ብድር የሰጠኝ ተቋም መንግሥታዊም ስለነበር እና እኔም ቦታውን ተቀብዬ አጠቃላይ ሂደቱን አጠናቀቄ ስለነበረ፤ የገንዘብ ብድሩን አልከለከሉኝም። ብሩን ተቀብዬ የተወሰኑ ማሽኖች ብገዛም ወደ ሥራው በደንብ ልገባ የቻልኩት በ2016 ዓ.ም ነው" ትላለች ስለ ሁኔታዋ በዝርዝር ስታስረዳ። ሙሉ እቃውን ለማሟላትም በተጨማሪነት ተቀጥራ ሥራ እንደጀመረች ትናገራለች።



ወጣት ብርሃን ቀነአ

ተቀጥራ ትሰራበት የነበረው ጫማ እና ቦርሳ አምራች ድርጅት ነበር። ከዛ በምታገኘው ገንዘብ የማሽን እዳዋን ትከፍላለች፣ በተጨማሪም የንግድ ፈቃድ አውጥታ ስለነበር ግብርም ትከፍላለች። አንዳንዴ ከምትሰራበት ቦታ ሥራዋን ጨርሳ ስትወጣ ወደ ራሷ መሥሪያ ቦታዋ በመምጣት የኪስ ቦርሳዎችን ትሰራ እንደነበር ትናገራለች።

"ወደ ቆዳ ምርት ውጤቶች ማምረት እንድገባ የተማርኩት ትምህርት በደንብ ጠቅሞኛል ብዬ አስባለሁ። ወደ ትምህርቱ ከመግባቴ በፊት በሀገራችን ጫማና ቦርሳ ይሰራል ብዬ አላስብም ነበር። ወደ ትምህርቱ ከገባሁ በኋላ ግንዛቤውን ሳገኝ እኔም መሥራት እችላለሁ የሚለው ሞራል መጣ። ተቀጥሬ መሥራቴ ደግሞ ሙያውን ለማዳበር የበለጠ ጠቅሞኛል" ስትል ትገልጻለች።

"ሥራውን ሥሰራ አንዳንድ ተግዳሮቶች ይገጠሙኛል" የምትለው ሥራ ፈጣሪዋ፤ ለምሳሌ አንድ ቦርሳ ሰው ላይ ብመለከት ለመሥራት ብፈልግ ቀጥታ እሱን መውሰድ አልችልም ዲዛይኑን ቀይሬ አዲስ ፈጠራ ጨምሬ ነው የምሠራው። ተመሳሳይ ብሠራ ገበያ ማጨናነቅ ነው የሚሆነው እንጂ ምርቱ አይሄድልኝም። ስለዚህ አዲስ ፈጠራ ደግሞ ጊዜ ወስዶ ማሰብ ስለሚፈልግ ትንሽ ያስቸግራል። " ትላለች።

"አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦችን ለማግኘት ማህበራዊ ሚዲያዎችን እከታተላለሁ፤ እዛ ላይ ያየሁትን በምን መልኩ ማሻሻል እንዳለብኝ አስቤ እሰራለሁ። ሌላው ደግሞ ከዚህ በፊት እኔ የሰራሁትን ሥራ እመለከትና ፎቶ አነሳለሁ ከዛን ቁጭ ብዬ ምን መጨመር እና መቀነስ እንዳለበት አስብና አዲስ ነገር ለመፍጠር እሞክራለሁ። " ስትል ትገልጻለች።

"መሥሪያ ቦታ ያለን ቢሆንም በልማት ምክንያት ውስጥ ለውስጥ መንገዶች ስለፈረሱ ምርቶቹን ደርድሮ ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው። መሽቶ ወደቤት ስንመለስ እቃዎቹን አንስተን ነው የምንሄደው። ቆዳ በባህሪው ደግሞ መጨማደድ አይፈልግም፤ አንድ ቦታ ተሰቅሎ አቧራውን ማራገፍ ብቻ ስለሚፈልግ ተሰብስቦ አንድ ቦታ ሲቀመጥ ይጨማደዳል" ትላለች።

የቆዳን ባህሪ አውቀው አመስግነው የሚገዙ እንዳሉ ሁሉ «ዋጋው ውድ ነው» የሚሉም አይጠፉም የምትለው ወጣት ብርሃን፤ ገበያ ላይ ቆዳ ከመወደዱ ጋር ተያይዞ ደንበኛው የሚፈልገው ዋጋ እና እቃዎቹ የሚቀርቡበት ዋጋ ተመጣጣኝ አለመሆን ሌላኛው ተግዳሮት መሆኑን ታነሳለች።

"ወደ ሥራው ከመግባቴ በፊት ኮሌጅ ያስተማረኝ መምህሬን አማክሬው ነበርና፤ ክፍለ ከተማዬ ባለበት ለመሥራት ባመለክት የተሻለ እንደሚሆን እና ማሽን ለመግዛትም ብድር በቀላሉ ማግኘት እንደምችል መክሮኛል። ሌላው ቆዳ እና ሌሎች ግብዓቶች የት እንደሚገኙ በአካባቢዬ ላይ የሚሰሩ ሰዎችን አጠያይቄ መርካቶ መሆኑን ነገሩኝ። ከዚህ በፊት ተቀጥሬ የምሰራበት አሰሪዬም ቦታውን ወስዶ አሳይቶኛል። " ትላለች።

ወደ ቆዳ ምርቶች ስትገባ "ግን ይሄን ነገር ትችይዋለሽ?" በማለት የሚጠይቁና ነገሮችን በጥርጣሬ ዓይን እንድትመለከት የሚገፋፉ ሃሳቦች ይቀርቡላት እንደነበሩ በማንሳት፤ ነገር ግን እራስን አሳምኖ ጨክኖ ከተገባበት የማይቻል ነገር አለመኖሩን ትጠቁማለች።

"እውነት ለመናገር እችላለሁ ብሎ እራስን ማሳመን ከተቻለ የማይቻል ነገር የለም። ከማህበረሰቡ የሚነገረውን ሁሉንም ሃሳብ ከተቀበልን ከባድ ነው። ነገር ግን ለራስ ሊጠቅም የሚችለውን ሃሳብ መርጦ መውሰድ ከተቻለ የሚጠቅም ሃሳብም አይጠፋም። " ስትል ትናገራለች።

አሁን ላይ ከመሥሪያ ቦታዋ በተጨማሪ፤ የተለያዩ ባዛሮች ሲዘጋጁ ምርቶቿን ለእይታና ሽያጭ ታቀርባለች። ተቀጥራ ከመሥራት ወደ መቅጠር በመሻገር ሁለት ሠራተኞችን አንድ በቋሚነት፣ አንድ ደግሞ በጊዚያዊነት ቀጥራ ታሰራለች። የገበያው ተቀባይነት መልካም የሚባል መሆኑን በመግለጽ፤ ምርቶቿን ለጅምላ ነጋዴዎች ታቀርባለች። የበለጠ ግን ባዛሮች ሲዘጋጁ ምርቶቿን በማቅረብ ተጠቃሚ መሆኗን ታስረዳለች።

ብርሃን ሥትሰራ ድካም የሌለባት ነው የሚመስለው፤ ደከመኝ እንቅልፌ መጣ ሳትል በምሽት ቦርሳም ሆነ ጫማ ሥትሰራ ነው የምትቆየው። በተለይ ደግሞ የተሰጣት ትእዛዝ ካለ ደንበኞቿን ላለማስከፋት ሌሊቱን ሙሉ ሥትሰራ ነው የምታድረው። ጠዋት ተነስታ ወደ ሱቅ ትወስዳለች። ምክንያቱም ለተሻለ ነገዋ መንገድ ከፋቹ ሥራና ሥራ ብቻ እንደሆነ ገብቷታል።

ቀጣይ እቅዷ ከዚህ የበለጠ በመሥራት አሁን የምትሠራበትን ቦታ በማስፋፋት፤ አሁን ቀጥራ ከምታሠራቸው ሠራተኞች በተጨማሪ፤ ሌሎች ሠራተኞችን በመቅጠር ምርት በስፋት አምርታ ወደ ውጭ ሀገራት የቆዳ ምርቶችን የመላክ ፍላጎት እንዳላት ታስረዳለች።

"ይህንን ህልሜን ለማሳካት ቦታ እና ገንዘብ በጣም አስፈላጊ ናቸው። በዚህ ረገድ አበዳሪ ተቋማት ብድር ማቅረብ ቢችሉ መልካም ነው። ሌላው ነገር ደግሞ ደንበኞችን ማግኘት ወሳኝ ነገር ነው። ምክንያቱ ምርቱ ከተመረተ በኋላ የሚገዛ ደንበኛ በስፋት ካለ ማደግ የማይቻልበት ምንም ምክንያት የለም" ትላለች።

ምርቶቿን ለማስተዋወቅ ባዛሮች ላይ ከማቅረብ ባለፈ፤ አንዳንድ ሥልጠናዎች ሲዘጋጁ ራሷን ለማስተዋወቅ መንገዶችን የምታገኝ ሲሆን፤ አንዳንድ ማህበራዊ ሚዲያዎችን በተወሰነ መልኩ ለመጠቀም ትጥራለች።

እንደ ወጣት ብርሃን ሃሳብ ወደ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ገብቶ መማር በጣም ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም የእጅ ሙያ መማር ያስችላል። ይህ ደግሞ ሙያው ከራስ ጋር ለዘላለም የሚቀር የትም ብሄዱ ከራስ ጋር የሚቆይ ነው።

ይህ ሁሉ ነገር ሊሆን የሚችለው የግል ጥረት የበለጠ ሲኖር ነው። የማህበረሰቡን አንዳንድ አሉታዊ ሃሳብ በመስማት ተስፋ መቁረጥ ካለ አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ የራስ አዕምሮ የሚለውን በማዳመጥ የማህበረሰቡን ሃሳብ ደግሞ መርጦ የተሻለውን መውሰድ አስፈላጊ ነው።

አብዛኞቻችን ሌሎች ስለመከሩን ብቻ የማንፈልገውን ትምህርት ነው የምንማረው። ከዚህ ይልቅ ውስጣችን የሚፈልገውን እንወቀው በዛ ለመቀጠል እንሞክር። ምክንያቱ አንድ ሰው ወዶት የሚማረው ትምህርት ሲሆን፤ በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ለመልፋት አይቸገርም። ሁሉም በተማሩበት ትምህርት በደንብ ቢሰሩ ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ትናገራለች።

እንደ ወጣት ብርሃን ገለፃ ኢትዮጵያ የእንስሳት ቆዳ በመላክ ታዋቂ ብትሆንም፤ እሴት ጨምሮ የቆዳ ምርቶችን በመላክ ረገድ ብዙም አልተሰራም። አሁን አሁን በተደረጉ ማሻሻያዎች ለውጦች እየታዩ ቢሆንም ገና ብዙ መስራትን ይጠይቃል። የተወሰኑ ምርቶች እየተላኩ ነው ያለው። እናም በዚህ ዘርፍ መሥራት ከተቻለ ከራስ አልፎ ሀገርንም ለመጥቀም እድል አለው።

ወጣት ብርሃን የግል ሥራ ስትጀምር ባጋጠማት ፈተና አልተንበረከከችም። ውጣ ውረዱ ሥራውን ትታ ተቀጣሪነትን እንድትመርጥ አላስገደዳትም። ይልቁኑ ፈተናዎቹን ወደ መልካም አጋጣሚ ቀይራቸዋለች። "እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ሲጠነክሩ ለምን ይህን ያህል አለፋለሁ የሚል ሃሳብ ይመጣል። ነገር ግን ከጎኔ አይዞሽ ይሄን ብትሰሪ ይሄ ይሆናል እያሉ የሚያበረታታ አይጠፋም። የእነሱን ማበረታቻ ቃል ስሰማ ደግሞ እበረታለሁ"ትላለች። ላጋጠማት ሁኔታ የሰጠችውን መፍትሔ እያብራራች።

ወጣት ብርሃን የእርሷ መለወጥ ሌሎች ዜጎችንም፣ ሀገርንም እንደሚጠቅም ታምናለች። በዚህ ምክንያት አሁን ካለችበት በተሻለ መሥራትን ትሻለች።

ከመንግሥትና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ማሽን ለመግዛት ብድር ቢመቻችላት፤ ከምንም በላይ ደግሞ ምርቶቿን የምትሸጥበት ቦታ ብታገኝ ከዚህም በተሻለ ውጤታማ እንደምትሆን ታምናለች። ይህንን ጥያቄዋን መንግሥት ምላሽ እንዲሰጣትም ትጠይቃለች።

በመጨረሻም አሁን ላይ ምርቶችን ወደ ክፍለ ሀገር ለመውሰድ በአንዳንድ ቦታዎች የሚከሰቱ የጸጥታ መደፍረስ ተግዳሮት በመሆናቸውና ለሁሉም ነገር ሰላም አስፈላጊ በመሆኑ ለሀገሯ ሰላምን እየተመኘች፤ በመጨረሻም ሥራዋን በምትሠራበት ወቅት በሃሳብም ሆነ በጉልበት ለደገፏት ምስጋናዋን አቅርባለች።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ስለትናንትን ሲነገር እንደ አዲስ ዘመን ያለ የታሪክ ማጣቀሻና ታሪክን ሰንዶ ለትውልድ አውራሽ አይገኝምና ታሪክ ነጋሪውን ካደመጡ ወጉ እልፍ ነው። “አዲስ አበባ ያብባል ገና” ይላልናም ከ1964ዓ.ም ገደማ ከታየው የማበብ ሰበዝ ለአብነት አንዱን ያሳየናል። በሌላ በኩል ደግሞ መቀሌን በጨረፍታ ምስል ያስቃኘናል። ከፓርላማው አዳራሽ ውስጥ የሆነው ነገርም ምን ነካቸው ሊያስብለን ነው። እጥር ምጥን ካሉት የጳውሎስ ኞኞ ደብዳቤዎች መካከልም ለራሱ ከተጻፉት ሁለቱን እናስታውሳለን።

**አዲስ አበባ ያብባል ገና**

የአዲስ አበባ ከተማ ባለፉት ጥቂት ዓመቶች ውስጥ ከፍ ያለ የዘመናዊነት መሻሻል አድርጋለች። ከዛሬ አሥር ዓመት በፊት አዲስ አበባ ከተማን ያየ ሰው ዛሬ እንደገና ተመልሶ ሲመለከት በተደረጉት ከፍተኛ የእድገት ለውጦች በጣም ይደነቃል። በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመቶች ውስጥ ያሳየችው የመሻሻል ለውጥ የሚደነቅ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ በየጊዜው ለሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ የአዲስ አበባ ከተማ ዓይነተኛ ምስክር ነች።

...

ከተማይቱ የተቆረቆረች ጊዜና ከዚያም በኋላ ያደረገችው እድገት የጊዜውን እንጂ ዘመናዊውን ፕላን ያልተከተለ ስለነበረ ዛሬ ማዘጋጃ ቤቱ ባሉት በቂ የተማሩ ሰዎች ከተማይቱ ወደ አዲስ ዘመናዊ ይዞታ ተለውጣለች።

...

በመንገድ ረገድም በየቀበሌው አዳዲስ መንገዶች በየጊዜው በመከፈታቸው የከተማይቱን መልክ ለውጠውታል።

...

ከዛሬ አሥር ዓመት በፊት በከተማይቱ የነበሩት መኪናዎች 20 ሺህ ሲሆኑ ዛሬ ግን ወደ 50 ሺህ ደርሰዋል። ለምሳሌ ያህል የቸርችል ጎዳናን በዘመናዊ ሁኔታ ለማሠራትና ለማስፋፋት ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ሲደረግበት፤ አዲስ ለሚሠሩት የመስፍን ሐረር መንገድና ለቄራ መንገድ በጠቅላላው ከሁለት ሚሊዮን ተኩል ያላነሰ ወጪ ተመድቧል።

(አዲስ ዘመን ታህሳስ 14 ቀን 1964ዓ.ም)

**መቀሌ ውብና ታሪካዊት ሰሜናዊ ከተማ ናት**

የትግሬ ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ የሆነችው መቀሌ ወለል ባለ ሜዳ ላይ እየተስፋፋች የምትሔድ መዲና ስትሆን በስተ ምሥራቅ ደቡብ በኩል የእንዳ ኢየሱስ ተራራ በኃይለኛ አውሎ ነፋስ ይከልላታል። ዙሪያውን በተራራ ባለመከበቧ ከተማዋ ነፋሻ ናት።

...

የአብርሃ ሕንጻ በብዙዎቹ እንደሚጠራው ታላቁ የከተማው ሆቴል በመሆን “የመቀሌ ሒልተን” የሚል ስም ተሰጥቷታል።

የትግሬ ሕዝብ ባሕላዊ ለውጥን በቀላሉ የሚቀበል አይመስልም። ብዙ ዘመናዊያን በሚታዩበት በመቀሌ ከተማ እንኳ ሴቶች በጥንታዊ የፀጉር ሥራ ማለት ሹርባ ተውበው ከዚያ ከሚያምረው ፀጉራቸው ላይ ቀጭን ኩታቸውን ጣል አርገው ይሔዳሉ። ወንዶችም ብዙዎቹ ጥንታዊውን ግማሽ ተፈሪ ሱሪ ቅድ ታጥቀው ሲታዩ፤ የዘመኑን አለባበስ ተቀብለናል የሚሉትም ካማረው ሱፍ ላይ ኩታ ደርበው ይታያሉ።

ሆኖም እንደኔ ላለ ከአዲስ አበባ የዘመናዊ ሥልጣኔ ደቀ መዝሙር ነኝ ብላ የምታምን ወጣት አጭር ልብስ ለብሳ ብትንሸራሸር የተቃውሞ ድምጽ የሚያሰማ የለም። ምናልባት የመቀሌ ከተማ ሰዎች የራሳቸውን የአለባበስ ባሕል እንደሚጠብቁ ሁሉ ሁሉም በየፊናው እንደፈለገው ይሁን የሚል ፍልስፍና ይከተሉ ይሆን?

( አዲስ ዘመን መጋቢት 13 ቀን 1964ዓ.ም)

**ከፓርላማ**

የሕግ መምሪያ ምክር ቤት በየሳምንቱ እንደተለመደው ሁሉ ትናንት ከአማካሪዎች በቀረቡት የሕዝብ ጉዳዮች ለመነጋገር ተሰባስቦ ሳለ፤ በአንዱ አባልና በሰብሳቢው ፕሬዚዳንት መካከል በአንዳንድ ጉዳይ ላይ በተፈጠረው ክርክርና አለመግባባት ምክንያት በፀጥታ ሊሠራ ስላልቻለ፤ የዕለቱ ጉባኤ ተበትኗል።

ምክር ቤቱ እንዲነጋገርባቸው ሃሳብ ካቀረቡት አባሎች አንዱ በሆኑት በተከበሩ አቶ ዘውዴ በዳዳ የደቡብ አዲስ አበባ ሕዝብ እንደራሴና በዕለቱ ሰብሳቢ ፕሬዚዳንት መካከል በምክር ቤቱ ውስጥ በተፈጠረው አለመግባባትና ክርክር፤ የዕለቱ ስብሰባ የተበተነ መሆኑን ሰብሳቢው ፕሬዚዳንት የተከበሩ አቶ ተክሊት መኮንን አስታውቀዋል።

በተከበሩት አቶ ዘውዴ በዳዳና በሰብሳቢው ፕሬዚዳንት መካከል አለመግባባት የተፈጠረው፤ ፕሬዚዳንቱ የሰጡትን ውሳኔ አማካሪው ጉባኤው ካልወሰነ በቀር የፕሬዚዳንቱን ትእዛዝ አልቀበልም በማለታቸው ነው። ሆኖም በዚሁ ምክንያት ምክር ቤቱ ውስጥ ፀጥታ በመታጣቱና ጉባኤውን ለመምራት ስላልተቻለ፤ የዕለቱ ስብሰባ እንዲበተን የተደረገ መሆኑ ታውቋል።

(አዲስ ዘመን ሰኔ 18 ቀን 1964ዓ.ም)

**አንድ ጥያቄ አለኝ**

-ይድረስ ለጳውሎስ ኞኞ

*ስምህን እንጂ መልክህን የማያውቅ ብዙ ነው። ስለዚህ አጠገባቸው መሆንህን ሳያውቁ ስላንተ አንሥተው ሲያሙህና ሲያመሰግኑህ አጋጥሞህ ያውቃል?

**ከፈለው አርጋው**

-ብዙ ጊዜ ነው። እንዲያውም አንዳንዶቹ “ና ጳውሎስን እናሳይህ” እያሉ ሲያንከራትቱኝ የሚያድሩ አሉ። አንዳንዱም የአደባደቡን ሁኔታ እንዲህ አድርጌ ደበደብሁት እያለ ለኔው ለራሴ አጫውቶኛል። እንዲህ ዓይነቱን ባወራው ብዙ ዓምድ ይፈጃል። ብዙ ወሽካቶች አሉ።

*ሚያዝያ 24 ቀን በወጣው ኢትዮጵያን ሄራልድ ጋዜጣ ላይ አቶ ኑሬ በፈቃዱ የተባሉ የማዘጋጃ ቤት ሠራተኛ ስለደመ መራራ ቴያትር በሰጠኸው ትችት የሰጡትን መልስ አንብቤአለሁ። አንተ በአማርኛ እንደጻፍከው በአማርኛ በሚወጡት ጋዜጦች ቢጽፉ ምን ይጎድላቸው ነበር? ምናልባት ኢትዮጵያዊ ሆነው አማርኛ የማይችሉ ከሆነ፤ ያንተን ትችት አንብበው እንዴት ለመረዳት ቻሉ? ወይስ የማያውቁት ሀገር ከሚናፍቋቸው ሰዎች አንዱ ሆነው? አስተያየትህን እጠብቃለሁ።

**አብደላ መሐመድ(ከጎንደር)**

-ግራ ለማጋባት ነው። ስለኔ አርቲክል ምንም ነገር የማያውቁት ፈረንጆች የምን ሕልም ነው ብለው እንዲሉ ካልሆነ በስተቀር ምናለ የኔን ያነበቡ ጥፋቴን እንዲያውቁልኝ ለአነበቡት ቢጻፍ? ግን ጽሑፉ የማይረባ መሆኑን ያወቅሁት “ያንባቢን ጊዜ አባከንክ” ተብዬ መወቀሴን ሳይ ነው። ምክንያቱም የኔ ጽሑፍ ጊዜ ማባከን ሳይሆን ብዙ ትምህርት የነበረበት ነውና ነው። ብዙ ነገሮች የተፈለሰፈበትን ጊዜና የፈልሳፊውንም ስም ይነገር ነበርና ነው።

(አዲስ ዘመን ሰኔ 24 ቀን 1964ዓ.ም)

# ዓለም አቀፍ

## ደቡብ ኮሪያዊው ክብደት በመጨመር የውትድርና ሥልጠና ለማምለጥ ሞክሯል ተብሎ ተቀጣ

የደቡብ ኮሪያ ፍርድ ቤት ክብደት በመጨመር የግዴታ የውትድርና ሥልጠና ለማምለጥ ሞክሯል ያለውን ግለሰብ ጥፋተኛ ሲል ወሰነበት። የደቡብ ኮሪያ የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን እንደዘገቡት የ26 ዓመቱ ግለሰብ የአካል ብቃት መለኪያ ጊዜው ሲደርስ ያገኘውን ጠራርጎ በመብላት ክብደት ጨምሯል ሲል የሴዑል ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ብሎታል።

ሰውዬው ክብደቱ ከመጠን በላይ በመሆኑ ምክንያት ከውትድርና ውጭ በሆኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሲያገለግል ቆይቷል። ግለሰቡ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ የአንድ ዓመት ቅጣት ተላልፎበታል። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሌላ ጥፋት አጥፍቶ ከተገኘ እስር ሊጠብቀው ይችላል ማለት ነው።

በቀን የሚመገበውን ምግብ መጠን እጥፍ በማድረግ ክብደቱን እንዲጨምር የመከረው ጓደኛው ደግሞ የስድስት ወራት ቅጣት ተፈርዶበታል ሲል ኮሪያን ሔራልድ ዘግቧል። ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ እና አካላዊ መሥራት የሚችል ኮሪያዊያን በመከላከያ ሠራዊት ለ18 ወራት የማገልገል ግዴታ አለባቸው።

ግለሰቡ መጀመሪያ ለወታደራዊ ሥልጠና ሲመዘገብ አካላዊ ብቃቱ ለሥልጠናው ብቁ የሚያደርገው ነበር። ነገር ግን ባለፈው ዓመት ለመጨረሻ ፈተና በተጠራ ጊዜ ክብደቱ 102 ኪሎ ግራም ደርሶ ስለነበር ነው ከሥልጠናው የታገደው። ደቡብ ኮሪያ በየትኛውም ጊዜ ከሰሜን ኮሪያ ጥቃት ሊቃጣብኝ ይችላል በማለት ነው ዜጎች የግዳጅ ወታደራዊ ሥልጠና እንዲወስዱ የምታደርገው።

ቢሆንም በኦሊምፒክ ሜዳሊያ ያመጡ፤ ሙዚቀኞች እና ሌሎች ሀገራቸውን ያስጠሩ ኮሪያዊያን ሥልጠናው ሊያልፋቸው ይችላል። ደቡብ ኮሪያ እና ዩናይትድ ስቴትስ ከኒውክሌር የጦር መሣሪያ ባለቤቷ ሰሜን ኮሪያ የሚመጣን አደጋ ለመከላከል በሚል በተለያዩ ጊዜያት የጋራ ወታደራዊ ሥልጠናዎች ያደርጋሉ ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።



## አንድ የጭነት አውሮፕላን ተከስክሶ በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት አደረሰ

የዲ ኤች ኤል የጭነት አውሮፕላን በሊዩቲኒያ ተከስክሶ የአንድ ሰው ሕይወት ሲያልፍ በሦስት ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱ ተነግሯል። ቦይንግ 737-400 የጭነት አውሮፕላኑ ከጀርመን ሌፐዚሽ ከተማ ተነስቶ በሉቱኒያ ዋና ከተማ ወደሚገኘው አውሮፕላን ማረፊያ ሲቃረብ ነው በአቅራቢያው በሚገኝ አንድ ቤት ላይ ተከስክሶ አደጋው የደረሰው።

የሀገሪቱ ባለሥልጣናት የአደጋው መንስኤ እስካሁን አለመታወቁን ገልጸዋል። በተከሰከሰበት ቤት ዙሪያ ያሉ መሠረተ ልማቶች በእሳት የተጎዱ ቢሆንም፤ በአካባቢው ያሉ ሰዎችን ማትረፍ መቻሉን የሀገሪቱ ባለሥልጣናት ተናግረዋል።

አውሮፕላኑ ከተከሰከሰ በኋላ በእሳት የተያያዘ ሲሆን አንድ የበረራ ቡድኑ አባል ሕይወቱ ማለፉን የሊዩቲኒያ ባለሥልጣናትን ጠቅሶ ሲኤንኤን ዘግቧል። አብራሪውን ጨምሮ ሶስት የበረራ ቡድኑ



አባላትም ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ሆስፒታል መወሰዳቸው ተገልጿል። ከጀርመኗ ላይፐዚሽ የተነሳው የጭነት አውሮፕላን የተከሰከሰበት መንስኤ እየተጣራ መሆኑንም የሊዩቲኒያ የብሄራዊ አደጋ አስተዳደር ኃላፊው ቪልማንታስ ቪልካውካስ ተናግረዋል።

አውሮፕላኑ ከመከስከሱ አስቀድሞ ፍንዳታ እንደገጠመው የሚያመላክቱ ጉዳዮች እስካሁን ሪፖርት አለመደረጋቸውንም ነው ለሀገሪቱ ብሔራዊ የዜና አገልግሎት ኤልአርቲ የገለጹት። በአውሮፕላኑ ከተገጨው መኖሪያ ቤት ውስጥ 12 ሰዎችን ለማስወጣት የአደጋ ጊዜ ሠራተኞች ርብርብ ማድረጋቸው ተሰምቷል። የቪሊኒየስ አውሮፕላን ማረፊያ የእሳት አደጋ ሠራተኞች በእሳት የተያያዘው አውሮፕላን ሙሉ በሙሉ እንዳይወድም ጥረት እያደረጉ ነው ተብሏል።

አደጋው በቪሊኒየስ ኤርፖርት የበርካታ አውሮፕላኖች የመነሻ ሰዓት እንዲጓተት ማድረጉ ቢገለጽም የአውሮፕላን ማረፊያው ቃል አቀባይ ግን ሁሉም በረራዎች በተያዘላቸው ሰዓትት ቀጥለዋል ሲል አል ዐይን ገልጿል።

# ስፖርት





## ኢትዮጵያ በአፍሪካ ሚሊታሪ ስፖርት ውድድር ሜዳሊያዎች ሰብስባለች

ዓለማየሁ ግዛው

በናይጄሪያ ዋና ከተማ አቢጃን አስተናጋጅነት ለሁለተኛ ጊዜ በመካሄድ ላይ በሚገኘው የአፍሪካ ጦር ኃይሎች (ሚሊታሪ) ስፖርት ፌስቲቫል ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ አስመዝግባለች። ሃምሳ አለቃ ወርቅውሃ ጌታቸው ሜዳሊያውን ያጠለቀች አትሌት ነች። በውድድሩ ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የተወጣጡ የጦር ኃይሎች እየተሳተፉ ሲሆን ኢትዮጵያ በመቻል ስፖርት ክለብ አማካኝነት ተወክላለች።

ውድድሩ ከኅዳር 11 ጀምሮ በምዕራብ አፍሪካዊቷ ሀገር ናይጄሪያ እየተካሄደ ሲሆን፣ በዋና ከተማዋ አቢጃን የሚገኘው ሞሾድ አብዮላ ናሽናል ስታድየም ፉክክሮችን እያስተናገደ ይገኛል። ኢትዮጵያ በመቻል ስፖርት ክለብ በመወከል ጠንካራ ተፎካካሪ መሆን የቻለች ሲሆን እስከ ትናንት ከሰዓት አራት ሜዳሊዎችን ሰብስባለች። በአትሌቲክስ ስፖርት እየተሳተፈ የሚገኘው መቻል፣ በአትሌት ሃምሳ አለቃ ወርቅውሃ ጌታቸው አማካኝነት የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ አሳክቷል።

አትሌት ሃምሳ አለቃ ወርቅውሃ ጌታቸው በ5 ሺ ሜትር ውድድር አሸናፊ የሆነችው በውድድሩ ጠንካራ ፉክክር በማድረግና በጥሩ ብቃት ተፎካካሪዎችን በመርታት ነው። ሌላኛዋ አትሌት ሃምሳ አለቃ አያልፍም ዳኛቸው በዚሁ ውድድር የብር ሜዳሊያ ማሳካት ችላለች።

በተጨማሪም በሜዳ ተግባራት የአትሌቲክስ ውድድሮች የተሳተፉ ሁለት አትሌቶች ሁለት የብር ሜዳሊያዎችን አስመዝግበዋል። በሴቶች ርዝመት ዝላይ ምክትል አስር አለቃ በፀሎት ዓለማየሁ የብር ሜዳሊያ ስታስመዘግብ፣ በተመሳሳይ በዲስከስ ውርወራ አስር አለቃ ዙርጋ ኡስማን የብር ሜዳሊያ አጥልቃለች። መቻል ስፖርት ክለብ እስከ አሁን በተሳተፈበት አትሌቲክስ ውድድር አንድ የወርቅ እና ሦስት የብር ሜዳሊያዎችን መሰብሰብ ችሏል።



**በአሕጉራዊው የሚሊተሪ ስፖርት ውድድር ኢትዮጵያ እስከ ትናንት አራት ሜዳሊያ አስመዝግባለች፣**

መቻል ስፖርት ክለብ በውድድሩ በአትሌቲክስ ስፖርት እየተሳተፈ የሚገኝ ሲሆን በአጭር ርቀት፣ መካከለኛ ርቀት፣ በሜዳ ተግባራት፣ በረጅም ርቀትና በማራቶን ውድድር እንደሚፎካከር ታውቋል። ክለቡ ለውድድሩ በሀገር ውስጥ ጠንካራ ዝግጅት በማድረግ፣ አትሌቶችንና አሠልጣኞችን ጨምሮ አርባ የሚደርሱ ልዑካን ቡድን አባላትን አካቶ ወደ ስፍራው አንዳቀና ለማወቅ ተችሏል።

የአፍሪካ ጦር ኃይሎች (ሚሊታሪ) ስፖርታዊ ውድድር በርካታ ስፖርቶችን በማካተት ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በተወጣጡ ሚሊታሪ አትሌቶች መካከል የሚካሄድ ውድድር ነው። የመጀመሪያው የአፍሪካ ሚሊታሪ ስፖርት ውድድር እአአ በ2002 ከዓለም አቀፉ ሚሊታሪ ካውንስልና ከአፍሪካ ሚሊታሪ ስፖርት ተቋም ጋር በትብብር በኬንያ ናይሮቢ አስተናጋጅነት ተካሂዷል። በመጀመሪያው የሚሊታሪ ስፖርት ውድድር 32 ሀገራት የተሳተፉ ሲሆን አራቱ በታዛቢነት ቀርበውም ነበር። አፍሪካ የሚሊታሪ ስፖርት ውድድርን በተለያዩ ስፖርቶች በማሰናዳት የመጀመሪያዋ አሕጉር እንደመሆንዋ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ተካሂዶ የነበረውን ውድድር በርካታ ታዋቂ የፖለቲካና የስፖርት ሰዎች እንደተከታተሉት መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የውድድሩ ዓላማ በአሕጉራቱ ለሚገኙ የሚሊተሪ ስፖርተኞች የውድድር ዕድል መፍጠር ሲሆን፣ አትሌቲክስን ጨምሮ፣ በቅርጫት ኳስ፣ ቦክስ፣ እግር ኳስ፣ ጎልፍ፣ እጅ ኳስ፣ ጁዶ፣ ውኃ ዋና፣ ቴኳንዶ፣ መረብ ኳስና በሌሎች ስፖርቶች ይከናወናል።

በናይጄሪያ አስተናጋጅነት በሚካሄደው ስፖርት ፌስቲቫል ኢትዮጵያን ጨምሮ በአጠቃላይ ከ25 የአፍሪካ አገራት የተወጣጡ 1 ሺህ 625 ስፖርተኞች በ 19 የስፖርት ዓይነቶች ተሳታፊ መሆናቸውም ተገልጿል። የስፖርት ፌስቲቫሉ ዛሬ ስድስተኛ ቀኑን የያዘ ሲሆን በመጪው ቅዳሜ ፍጻሜውን ያገኛል ተብሎ ይጠበቃል። ፌስቲቫሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በኬንያ አስተናጋጅነት ከተካሄደ ከ20 ዓመታት በኋላ በድጋሚ መካሄድ ችሏል።

ውድድሩ በአፍሪካ ውስጥ ለሚገኙ የሚሊታሪ ቡድኖች ያላቸውን ተሰጥዖ ለማሳየት ዕድል እንደሚፈጥር የታመነበት ሲሆን መድረኩ ለስፖርተኞቹ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመፎካከርና ከተቀኑት የአፍሪካ ሀገራት ጋር የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ተጠቁሟል። በተጨማሪም በጦር ኃይሉ ውስጥ የአካል ብቃት እና የስፖርት እድገትን ከማጠናከርም በላይ ውድድሩ የአፍሪካ ሀገራትን የግዛት ወሰን ለመጠበቅ በሚደረገው ሥራ ክልላዊ ትብብር እና ውሕደትን ለማሳደግ ያለመ ነው ተብሏል።

በዘንድሮው የጦር ኃይሎች (ሚሊታሪ) ጨዋታዎች አልጄሪያ፣ ካሜሩን፣ ግብፅ፣ ኢትዮጵያ፣ ጋና፣ ኬንያ፣ ሞሮኮ፣ ደቡብ አፍሪካ እና አስተናጋጇ ናይጄሪያ ከተሳታፊ ሀገራት መካከል ይጠቀሳሉ።


## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በአ/ብ/ክ/መ በደ/ወ/ዞን የደሴ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት ለመ/ቤቱ አገልግሎት የሚውሉ

- ደንብ ልብስ ግዥ
- ህትመት ማሳተም
- ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ግዥ
- ጽህፈት መሳሪያ ግዥ
- አላቂ ቋሚ እቃዎች ግዥ
- ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ጥገና
- ፈርኒቸር ግዥ
- ፅዳት እቃዎች ግዥ
- ፈርኒቸር/ ቢሮ እቃዎች ጥገና
- መስተንግዶ ግዥ

ከላይ የተዘረዘሩትን እቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች በጨረታው መወዳደር የሚችሉ መሆኑን ይጋብዛል፡፡

1. በዘመኑ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ማስረጃ ያላቸው፡፡
2. የግብር ከፋይ መለያ (TIN) ቁጥር ማስረጃ ያላቸው።
3. የግዥ መጠን ከብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ እና በላይ ከሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ
4. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ 1-3 የተጠቀሱትና የሚመለከታቸውን ማስረጃ ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው።
5. ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ በደሴ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት ግዥ/ፋ/ንብ/አስ/ደ የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 06 የሚገዙ እቃዎችን ዓይነትና ዝርዝር መግለጫ /ስፔስፊኬሽን/ ከጨረታ ሰነዱ ማግኘት ይችላሉ፡፡
6. ተጫራቾች የተዘረዘሩትን የጨረታ ሰነዶች የማይመለስ ብር 50.00 /ሀምሳ ብር/ በመክፈል በደሴ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት ግዥ/ፋ/ንብ/አስ/ደ/ጋፊ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 06 በመገኘት መግዛት ይቻላል፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በሞሉት ዋጋ ከነቫቱ 2% በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
8. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሰነዱን አንድ ፖስታ ከነ ኮፒው በጥንቃቄ ታሽጎ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው ቀን ድረስ ግ/ፋ/ንብ/አስ/ደ/የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 06 በተዘጋጀው ጨረታ ሳጥን ውስጥ ዘወትር በስራ ሰዓት እስከ ቀኑ 11:00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
9. የጨረታ ሳጥን ታሽጎ በ16ኛው ቀን ማለትም ከጠዋቱ በ4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በደሴ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት ግ/ፋ/ንብ/አስ/ደ/የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 06 ይከፈታል፡፡
10. መ/ቤቱ በሎት ዋጋ የማወዳደር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
11. መ/ቤቱ በጨረታ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ስበስጠ መረጃ፡**- መ/ቤቱ በአካል መቅረብ ወይም በስልክ ቁ 033 111 6552 ወይም 033 3110003

**በአ/ብ/ክ/መ በደ/ወ/ዞን የደሴ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት**